

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

የሶዶ ክስታኔ ማህበረሰብ የሸባል (የሰርግ) ስርአት ከሙዚቃዊ ተውኔት አንጻር።

በ

አንዱዓለም እንዳሻው

ለአርትስ ኦፍ ባችለር ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

ወልቂጤ ኢትዮጵያ

ነሃሴ 2013 ዓ.ም

የሶዶ ክስታኔ ማህበረሰብ የሸባል (የሰርግ) ስርአት ከሙዚቃዊ ተውኔት አንጻር።

በ

አንዱዓለም እንዳሻው

የጥናቱ አማካሪ

ዳናይት ብርሃኑ

ለአርትስ ኦፍ ባችለር ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

ወልቂጤ ኢትዮጵያ

ነሃሴ 2013 ዓ.ም

የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥንታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአተር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማማከሪያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪው ስም.....ፊርማ.....

ይህ በተማሪ አንዱዓለም እንዳሻው "የሶዶ ክስታኔ ማህበረሰብ የሸባል(የሰርግ ስርአት) ከሙዚቃዊ ተውኔት አንጻር" በሚል ርዕስ የተሰራውን የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥንታዊ ፅሑፍ የዩኒቨርስቲውን ጥራት ደረጃ ያሟላ እና ለቴአተር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነው።ይህም በፈታኝ ኮሚቴ ተረጋግጧል።

ፈታኝ1 **ፊርማ**

....

ፈታኝ2 **ፊርማ**

....

ቀን.....

ምስጋና

ሁሉን ለሚችል ፈጣሪ ለመድሃኔአለም ከነ እናቱ ድንግል ማርያም!፣ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የትቴአትር ጥበባት ትምህርት መምህርት እንዲሁም የዚህ ጥናት አማካሪ ዳናዊት ብርሃኑ ይህ ጥናት በሚሰራበት ጊዜ መረጃ በመስጠትና ተገቢውን ትብብር ላደረጉልን የሶዶ ጉራጌ ባህልና ቱሪዝም እና ማህበረሰብ፣ ለወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ምስጋና ይሁን።

አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በሶዶ ክስታኔ ማህበረሰብ የሸባል (የሰርግ) ስርአትን ከሙዚቃዊ ተውኔት አንጻር የተሰራ ጥናት ነው። ይህም ማህበረሰቡ በሰርግ ወቅት ከሚጠቀሟቸው አልባሳት አንጻር፣ ከቁሳቁስና ከተውኔት አላባውያን አንጻር የተተነበት ሲሆን በታዩት ክፍተቶች ላይ የመፍትሔ ሀሳብ የተሰጠበት ነው።

ማውጫ

ምዕራፍ አንድ 1

1.1.መግቢያ 1

1.2 የጥናቱ ዳራ 1

1.2. የጥናቱ አላማ 2

1.2.1. የጥናቱ ዓብይ አላማ 2

1.2.3. የጥናቱ ንዑስ አላማ 2

1.2.4. የጥናቱ ጠቀሜታ 2

1.2.5. የጥናቱ መጠነ ርዕይ 3

1.2.6. የጥናቱ ዘዴ 3

1.2.6.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች 4

1.2.7.የጥናቱ አወቃቀር 4

1.2.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸው 4

ምዕራፍ ሁለት 5

2.ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት 6

2.1.1. የትውልት ምንነት 6

2.1.2. ሽባል ወይም ሰርግ 7

2.1.3.ቴአትር 8

2.1.5.ሙዚቃዊ ቴአትር 9

2.2. ሙዚቃዊ ተውኔት አላባዎች 9

2.2.1. ሙዚቃ 10

2.2.2. ውዝዋዜ 11

2.2.3. መቼት 11

2.2.4. ገፀ-ባህሪ 13

2.2.6.ጭብጥ 14
2.2.7.አልባሳት 15
2.2.8.ቃለ ተውኔት 16
2.2.9.ቁሳቁስ 17
2.3. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት 18
ምዕራፍ ሶስት 19
3.የመረጃ ትንተና 19
3.1.የጉራጌ ማህበረ ሰብ ታሪካዊ አመጣጥ 19
3.1.1. የህዝብ አሰፋፈር እና መልከዓ ምድር 20
3.1.2. በቤተ ጉራጌ የሶዶ ክስታኔ ብሔረ-ሰብ 21
3.2. ባህላዊ ሽባል [ሰርግ] በክስታኔ 21
3.2.1. ቸግ 22
3.2.2.በቸግ ቀን የሚደረጉ ጨዋታዎች 22
3.2.3. ጥፍር ቀፈፋ 22
3.2.4. የእንጨት ፈለጣ ቀን 23
3.2.5. የጌሾ ወቀጣ ቀን 24
3.2.6.የከሶ ቀን 24
3.2.7. የእንሾሽላ ቀን 24
3.2.8.የሰርግ ቀን 26
3.2.9. የብርንዶ ስአት 27
3.2.10. የሰርጉ ማጠቃለያ 27
3.3. የሽባል ስርአት ከሙዚቃዊ ተውኔት ንፅፅር 28

3.3.1.ሙዚቃ 28
3.3.2. ውዝዋዜ 29
3.3.2.1 በቡድን የሚደረጉ ዉዝዋዜ 30
3.3.3. ሴራ 30
3.3.5.ጭብጥ በሸባል 30
3.3.6.ዓብይ ጭብጥ 30
3.3.7.ንዑሳን ጭብጥ 31
3.3.8.ገፀ-ባህርያት በሸባል 31
3.3.9 አልባሳት 32
3.3.10 ቃለ- ተዉኔት 33
3.3.11 ቁሳቁስ 33
3.3.12. መቼት 34
ምዕራፍ አራት 36
4.ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳቦች 36
4.1. ማጠቃለያ 36
4.2. የመፍትሄ ሃሳቦች 36
ዋቢ-መጻህፍት 39

ምዕራፍ አንድ

1.1.መግቢያ

አለማችን የእልፍ ቋንቋዎች ባለቤት ነች ኢትዮጵያ ሃገራችንም ከሰማንያ በላይ ብሔር ብሔረሰቦች የሚኖሩባት ህብረ-ብሔራዊት ሀገር መሆኗ ይታወቃል፡፡, እነዚህም ህዝቦቿ ማንነታቸዉ ደምቆ እና ተዉቦ አንደኛዉ ከሌላኛዉ ጋር በባህላቸዉ እና በታሪካቸዉ ተሳስረዉ ለዘመናት አብረዉ የኖሩ፤ አንዱ ማህበረሰብ ከሌላዉ ማህበረሰብ የሚለዩበት የራሳቸዉ መገለጫዎች ወይም እሴቶች አሏቸዉ፡፡ በመካከላቸዉም የባህል መወራረሰ ቢኖርም እንደ ክዋኔዉ ሰርዓትና ሁኔታ ያለዉን ልዩነት በመቻቻል እና በልዩነት ዉስጥ አንድነት ፈጥረዉ ህብረ ብሔሮች ተሳስበዉ እና ተከባብረዉ ሲኖሩ በአኗኗር ልዩነት ምክንያት አንዱ ሐዘኑን፣ ሌላዉ ደስታዉን፣ አንዱ ለቡድኑ ጥሩ ጊዜ ማስታወሻነት፣ ሌላዉ ደግሞ የቡድኑን ክፉ ጊዜ መታሰቢያ አድርጎ ይጠቀምበታል፡፡ ከነዚህ ህዝቦች መካከል በቤተ ጉራጌ የክስታኔ ማህበረሰብም በርካታ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ እሴቶች ባለቤት ነዉ፡፡ በማህበረሰቡ ወስጥ፣ሀገረሰባዊ የእርቅ ስነ-ስርዓቶች፣ የለቅሶ ስርአቶች፣ የሰርግ ስርአቶች፣ ኬርታ፣ ሽንጎ፣ ግቦ፣ አዳብና ጥቂቶቹ ናቸዉ፡ ይሄ ጥናታዊ ጽሁፍም ከነዚሁ ትውፊቶች ዉስጥ የሶዶ ጉራጌ ትውፊታዊ የሽባል ወይም የሰርግ ስነ- ስርአት ከሙዚቃዊ ተውኔት አንጻር ምን ይመስላል የሚለውን ቃኝቷል፡፡

1.2 የጥናቱ ዳራ

አጥኚው ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ለመስራት ያነሳሳው በአከባቢው ለየት ያለ የሰርግ [ሽባል] ስርዓት መኖሩንና ትውፊቱ እየጠፋ ወይም እየተሸረሸረ መሆኑን በመገንዘቡ፣ ስለ ሽባል ስርዓት የተጠና ጥናት ባለመኖሩ፣ ይህ ጥናት አካባቢውን ለማስተዋወቅ ከፍተኛ ድርሻ እንደሚኖረው በመገንዘቡ፤ የሽባል ስርዓት በዉስጡ የሙዚቃዊ ተውኔት አላባዎችን መያዙን በመገንዘቡ፣ አጥኚው በማህበረሰቡ ውስጥ በማደጉ እና ስርዓቱ በሚከወንበት ወቅት በተደጋጋሚ ክዋኔው ላይ በመገኘቱ እንዲሁም በነዚህ ክዋኔዎች ላይ ያሉትን ድርጊቶች በመመልከቱ ነው፡፡ ይህም ማለት በክዋኔው ወቅት ላይ ሰርገኞች ሰርጉን ጀምረው እስኪያጠናቅቁ ድረስ ሙሽሪትና ሙሽራው ሳይተያዩ እስከ ሰርጋቸው ማጠናቀቅያ ድረስ መቆየታቸው፤ ሽማግሌዎች በክብር እስከ ሴት ልጅ ቤተሰብ ድረስ ነጭ ጋቢ ለብሰው መጠየቃቸው ፣ ሃሳባቸው ቢሳካላቸውም ባይሳካላቸውም መርቀው ብሎም ኬርታ አድርገው መመለሳቸው፣ የሚጠቀሟቸው ቁሳቁሶችና አልባሳት እንዲሁም በሰርጉ ወቅት የሚደረጉ ህብረ ዝማሬዎች ከሌሎች መዝሙሮች በተለየ ጉኔታ ለሙሽሮች ጽኑ

ፍቅር፣ ለሙሽሮች ቤተሰቦች መልካም የሆነ ቤተሰባዊ ዝምድና ለሃገር ሰላም ፣ እርስ በእርስ የመደጋገፍን ሁኔታዎች በመመልከቱ ነው።

1.2..8. ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

1. ሽባል ምንድነው?
2. በሶዶ ጉራጌ የክስታኔ ማህበረሰብ የሽባል [የሰርግ] ስነ- ስርአት ላይ ምን አይነት ክዋኔዎች ይከወናሉ?
3. የሶዶ ጉራጌ ማህበረሰብ የሰርግ ስነ- ስርአት ከሙዚቃዊ ተውኔት አንጻር እንዴት ቀርበዋል?

1.2. የጥናቱ አላማ

1.2.1. የጥናቱ ዓብይ አላማ

የሶዶ ጉራጌ ማህበረሰብ ትውፊታዊ የሽባል ወይም የሰርግ ስርአት ከሙዚቃዊ ተውኔት ጋር ንፅፅራዊ ትንተና መስጠት።

1.2.3. የጥናቱ ንዑስ አላማ

የሶዶ ጉራጌ ማህበረሰብ ትውፊታዊ የሽባል ወይም የሰርግ ስርአት ከሙዚቃዊ ተውኔት አላባውውያን አንጸር መተንተን።

የሶዶ ክስታኔ ማህበረሰብ ባህልን ለሌላው ማህበረሰብ ማስተዋወቅ::

1.2.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

- ትውፊቱ ወይም ሰርዓቱ በወረቀት ሰፍሮ ሳይበረዝ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ይጠቅማል፣
- በሰርግ እና በሌሎች የማህበረሰቡ ትዉፊቶች ላይ ተጨማሪ ጥናት ለማጥናት በአስጠኝዎች እና በአጥኝዎች ላይ መነሳሳትን ይፈጥራል።
- ከዚህ በፊት የሶዶ ጉራጌ ማህበረሰብ የሰርግ ስርአት ላይ የተደረገ ጥናት የለም። በመሆኑም የማህበረ-ሰቡንና የሰርግ ስርአቱን ምንነት እንዲታወቅና ለሌሎች አጥኝዎች እንደ መረጃነት ያገለግላል።

- ጥናታዊ ጽሑፍ ጠቀሜታ እንደ ግለሰብ ባህሉን የማሳወቅ፡እንደ ማህበረሰብ አከባቢውን በማሳወቅ እና እንደ ሀገር ሀገራችን ኢትዮጽያ ብዙ ያልተነኩ ባህሎች እንዳሏት ለማስገንዘብ ይጠቅማል።

1.2.5. የጥናቱ መጠነ ርዕይ

የዚህ ጥናታዊ ዉሑፍ መጠነ ርዕይ ወይም ወሰን በቤተ ጉራጌ የሶዶ ክስታኔ ማህበረሰብ በሶዶ ወረዳ ላይ የሚከወነውን ሽባል ወይም ሰርግ የተሰኘውን ትውፊት ከሙዚቃዊ ተውኔት አንጻር መተንተን ነው።

1.2.6. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም የተጠና ነው። ገላጭ የምርምር ዘዴን አለም እሸቱ “መሠረታዊ የምርምር እና የዘገባ ዘዴ” በተሰኘ መጽሃፍ ላይ እንዲህ ገልፆታል "ገላጭ ምርምር - ምን ? - ምንድነው ? እያለ ለማብራራት ይሞክራል። ገለፃን፣ ትንታኔን እና አተሮጓጎምን መሰረት የሚያደርግ ሲሆን በሁለት ተለዋዋጮች መካከል የሚኖረውን ተዛምዶ እያወዳደረ እና እያነፃፀረ ሊመለከት ይችላል። " (1994፣148)

የክስታኔ ትውፊታዊ የሽባል ክዋኔ የሚጠናበት የጥናት ዘዴም የ ገላጭ ምርምር ዘዴን ባህርያት የሚያሟላ ነው።ለምሳሌ፦ገላጭ የምርምር ዘዴ 'ምን-ምንድነው?' የሚለውን ጥያቄ ያነሳል። የክስታኔ ትውፊታዊ የሽባል ክዋኔን ጥናት ለመስራትም አጥኚው እነዚህን 'ምን? ምንድነው?' የሚለውን ጥያቄ በመጠየቅ የሚሰራ ይሆናል።እንዲሁም ገላጭ የምርምር ዘዴ በሁለት ተለዋዋጮች መካከል የሚኖረውን ተዛምዶ ሊመለከት ይችላል።አጥኚውም በሁለቱ ክዋኔዎች መካከል ያለውን ተዛምዶ እና ልዩነት እያወዳደረ የሚያጠና ይሆናል።

በተጨማሪም ገላጭ የምርምር ዘዴ መላምቶችን መቅረፅ እና መፈተሽን ያካትታል።ገላጭ የምርምር ዘዴ ቋሚ እና አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት ክስተቶችን ባሉበት ተፈጥሮአዊ አከባቢ ይመረምራል።እንዲሁም ተጨባጭ መረጃ ላይ በመመስረት ትክክለኛ መደምደምያዎችን ይሰጣል።አጥኚውም በዚህ ገላጭ የምርምር ዘዴ ላይ በመመርኮዝ ስለ ሽባል አጀማመር የሚከወኑትን ንግርት እና መላምቶች በመፈተሽ ተጨባጭ የሆኑ መረጃዎችን በማቅረብ ይሰራል።የገላጭ ምርምር ዘዴ ባህርያት(መገለጫዎች) ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ለመስራት የሚረዱ በመሆናቸው አጥኚው በገላጭ የምርምር ዘዴ ለመስራት መርጧል።

1.2.6.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑት መረጃዎች ለመሰብሰብ ምልከታ እና መዛግብትን ፣ እንዲሁም በባህሉ ላይ የተሰሩ የቪዲዮ እይታዎችን በመመልከት በቃለ መጥይቅ ተጠናክሮ በማቅረብ ተሰናድቷል። አለም እሸቱ መሰረታዊ የምርምር ዘገባ አጻጻፍ በሚለው መፅሃፍ ላይ ቃለ መጠይቅን እንዲህ ሲል አስቀምጦታል፡- *"ቃለ መጠይቅ ጠያቂው ከተጠያቂው ጋር በግንባር ተገናኝቶ በፅሁፍ ሳይሆን በቃለምልልስ መረጃ የሚሰጥበት ሂደት ነው። " [2006 ፣ 61]*

አጥኚው ቃለ መጠይቅን የመረጠበት ዓላማ መረጃዎች የጥናቱ ክፍል ከሆኑት የማህበረሰብ አካላት ጋር በመገናኘት ትውፊቱን በጥልቀት የሚያውቁት፣ የተማሩት እና ያልተማሩትንም ስለሚያሳትፍ ነው።

በመቀጠልም ምልከታን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል። ምልከታን አጥኚው የተጠቀመበት ምክንያት የአካባቢው ተወላጅ እና ባህሉን ስለሚያውቀው እና ለትውፊቱ ቅርብ ስለሆነ ምልከታን ሊጠቀም ችሏል።

1.2.7.የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በአራት ክፍሎች ይዋቀራል።ምዕራፍ አንድ መግቢያ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ ዓብይ አላማ፣ የጥናቱ ንዑስ አላማ፣ የጥናቱ አወቃቀር፣ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች እና በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች የሚሉትን ያካትታል። በምዕራፍ ሁለት በንድፈ ሀሳብ ቅኝት እና በተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት ላይ ያተኩራል።በምዕራፍ ሦስት በዋናነት የጥናቱ ክፍል የቀረበበት እና መረጃዎች ተተንትነው የሚቀርብበት ሲሆን በምዕራፍ አራት የጥናቱ መደምደምያ እና መፍትሔ ሀሳብ ይሰጥበታል ።

1.2.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸው

የዚህ ጥናት አጥኚ ጥናቱን በሚያካሄድበት ወቅት የተለያዩ ችግሮች ገጥመውታል። ከነዚህም መካከል፣ ጥናቱ የሚከናወነው በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ሲሆን ትውፊቱ የሚገኘው ደግሞ በሶዶ ወረዳ ውስጥ በመሆኑ በሁለቱ መካከል ያለው የቦታ ርቀት መረጃን በበቂ ሁኔታ እናዳይገኝ አድርጓል። በተጨማሪም ጥናቱ የሚካሄደበት ወቅት በማህበረሰቡ ዘንድ የሰርግ ክንውን አለመኖሩ ብሎም ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት በማህበረሰቡ ዘንድ የሰርግ ወቅት ያለመሆኑ፣ በክስታኔ ማህበረሰብ በትውፊታዊ በሽባል ወይም በሰርግ ስርአት ላይ የተሰሩ ሌሎች ጥናቶች ያለ መኖር ፣ከገጠሙት ችግሮች መካከል ይጠቀሳሉ። መረጃ ለማሰባሰብም ከተጠቀመባቸው

ዘዴዎች መካከል የማህበረሰቡን አካላት በስልክ በማነጋገርና ማህበረሰቡ የሚገኝበት ስፍራ ድረስ በመሄድ መረጃዎችን መሰብሰብ ችሏል፡፡ የሰርግ ወቅት ባለመሆኑ ምክኒያት የገጠመውን ችግር ለመቅረፍ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ አካላትን በማናገር እና የተለያዩ ያልታተሙ ፅሁፎችን በመቀበል እንደ መረጃ ምንጭነት በመጠቀም ችግሩን ለመፍታት ሞክሯል፡፡

ምዕራፍ ሁለት

2.ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

2.1 የክለሳ ድርሳናት

2.1.1. የትውፊት ምንነት

ባህል ወይም ትውፊት ማለት ካለፈው ትውልድ ወደ ሚቀጥለው ትውልድ የሚተላለፍ ዘመናትን ያስቆጠረ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖር ስረዓት ነው። ትውፊት አንዱ የማህበረሰቡ መገለጫ ከመሆኑ የተነሳ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ሰውች በሙሉ የትውፊት አካል ናቸው። ለዚህም ማጠናከሪያ እንዲሆን መልዓከ ሰላም ዳኛቸው እንዲህ ሲል አስቀምጦታል፡-*"ትውፊት ድርጊት ወይም እውነት ከአንድ ትውልድ የሚተላለፍ መሳሪያ ነው። " (ትውፊት እና መንፍሳዊ ህይወት ፣ 2004፤4 ዓ.ም።)*

ፅንሰ ሃሳቡ እንደሚያስረዳው ትውፊት ማለት ድርጊትን ወይም እውነትን ካለፈ ትውልድ ወደ የሚቀጥለው ትውልድ የሚያስተላልፍ መሳሪያ ነው። ትውፊት ከትውልድ ወደ ትውልድ በቅብብሎሽ የመጣ የማህበረሰቡ መገለጫ መሆኑን የሚያሳይ ነው። በተጨማሪም ትውፊት ማለት የአንድ ማህበረሰብ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ እና የአኗኗር ዘይቤን የሚንፀባረቅበት ክዋኔ ነው። *" ትውፊት ማለት ካለፈው ትውልድ ወይም ካለፈው ትውልድ የተወረሰ እና ዘመነኛ ደራሲዎች በጥናትና ምርምር የመረመሩበት እምነት፣ ስነቃል፣ አስተሳሰብ እና የመሳሰሉት ያካትታል።" (ተውኔታዊ መዝገበ ቃላትና ብያኔዎቻቸው፣ ዘሪሁን አስፋው ፣ 2004፤61)*

ይህ ማለት ትውፊት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ባህላዊ ክዋኔ ሲሆን በማህበረሰቡ እድገት እና ስልጣኔ ጋር እያደገ እና እየተሻሻለ የሚሄድ ነው። በማህበረሰቡ ተፈጥሮ ካለፈው ትውልድ ወደ ተከታዩ በቃል እየተላለፈ የመጣ መሆኑን ያስረዳል። *"ትውፊት ማለት አወፈየ ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ውርስ፣ ቅብብል ማለት ነው። ይህም አንድ ትውልድ (ሰው) ከሱ በፊት ከነበሩት የሚወርሰው፣ የሚያገኘው፣ የሚቀበለው ነገር ነው። ሂደቱም በዚህ የሚያበቃ ሳይሆን እርሱም በተራው ለተተኪው ያስተላልፋል። " (ዲቆን ሄኖክ ሃይሌ፤ ቤተ-ክርስትያንህን እወቅ ፣ 2001፤11ዓ.ም)*

በዚህም ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የአንድ ማህበረሰብ የእለት ተእለት መገልገያ መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግለው ማለትም እምነት፣ ባህል፣ ወግ፣ መረጃ ሲሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ

የሚተላለፍ ነው። በተለይም በቃላዊ ወይም በማህበረሰቡ ተግባቦት ጠቃሚም ይሁን ጎጂ በመስማት ወይም በማየት ካለፈው ትውልድ የሚረከበው ነገር ነው። ባህል ሁለንተናዊ ምሉዕነት ያለዉ ጽንሰ ሀሳብ ነዉ።ባህል የአንድን ማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ፣ማህበራዊ ክንዋኔዎቻቸውን ማለትም ባህላዊ የለቅሶ ስርዓቶችን ባህላዊ የጋብቻ ስርዓቶችን እና እሴቶቻቸውን በሙዚቃ፣ በሥዕል፣ በዉዝዋዜ፣ በስነ-ጽሑፍ የሚገለጥ ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው *"የባህል መሠረታዊ ሀሳብ የያዙት ከራሱ ከባለቤቱ የሰዉ ልጅ ተፈጥሯዊ ሰብዕና ጋር በማቆራኘት ነው።ማንም ሰው ራሱን ከባህሉ ነጥሎ ማውጣት አይችልም። ምክንያቱም ከባህሉ ጋር የተቆራኘ ነውና" (የጥበባት ጉባኤ ፣ ጌታቸው በለጠ ፣ 2004፣62 ዓ.ም)*

ከጥቅሱ የምንረዳው ማንም ሰው ራሱን ከባህሉ ነፃ አውጥቶ መኖር አይችልም። ያለመቻሉም ምክንያት የባህሉ አንድ አካል በመሆኑ እና ሙሉ በሙሉ ራሱን ከባህሉ ነጥሎ መኖር እጅግ ከባድ መሆኑንና ከእኛ ከሰዉ ልጆች ተፈጥሮኣዊ ስብዕናችን ከባህሉ ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ራሳችንን ከባህል ሙሉ በሙሉ ሸሽገን መኖር አንችልም ከዚህ የተነሳ ነው እንግዲህ ባህል ከሰው ተፈጥሮኣዊ ስብዕና ጋር የተቆራኘ ነው የሚባለው።ነገር ግን ሰው የሚስማማበትን ባህል እና ወግ ተቀብሎ እና ያልተስማማበትን ትቶ የመኖር መብት አለው።

2.1.2. ሽባል ወይም ሰርግ

በጉራጌ ዞን የሶዶ ወረዳ የባህልና ቱሪዝም ሃላፊ እንዳልካቸው ግዛው ሽባልን እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል "ሽባል ማለት ሰርግ ማለት ሲሆን በሶዶ ጉራጌ ማህበረ-ሰብ ቋንቋ የተሰጠው ስያሜ ነው። ብሎም የጋብቻ ስነስር አት ልንለው እንችላለን " ተጠያቂው እንደገለጹትም ከጥንት ጀምሮ ለአቅመ አዳም በደረሰ ወንድና ለአቅመ ሄዋን የደረሱ ሴት ልጆች ጥንዶች በጋራ ለመኖር የጥምረት ትእይንት ነው። የጋብቻ ሥነ ስርዓት ወይም **ሠርግ** የሠዎች የጋብቻ ሥርዓት እንደየ ባሕሉ እና ወጉ ይለያያል። **ባህላዊ** ወይንም በሌላ ተመሣሣይ ሥርዓት ውስጥ ለመተሳሰር ቃል የሚገቡበት ዝግጅት ነው። ሰርግ በሁሉም አለም በሰው ልጆች ሂዎት ውስጥ የሚከወን የደስታ ጊዜ ነው። ሰዎች ይጋባሉ ይህንኑ ለትውልድ ያስተላልፋሉ ።ይህም በቤተ ጉራጌ በሶዶ ክስታኔ ብሄረሰብ "ሽባል" ተብሎ ይጠራል።

በመጽሃፍ ቅዱስ "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም" ዘፍጥረት [1:27] ይህ ቃል የፈጣሪ ቃል ነው። ይህም ማለት ወንድ ልጅን ሴት ልጅ ታስፈልገዋለች ሴት ልጅን ወንድ ልጅ ያስፈልጋታል የሚል አንድምታ ያዘለ ነው። በመሆኑም የሰው ልጅ በተፈጥሮው ሶስት

ክስተቶችን ያስተናግዳል። እነርሱም ውልደት፣ እድገት እና ሞት ናቸው። የሰው ልጅ እነዚህን ሶስት የተፈጥሮ ክስተቶች ያስተናግድ ዘንድ የትውልድ መምጣትን እና መሄድን ለማስቀጠል ሰዎች ከተቃራኒ ፆታቸው ጋር ወይም ተባዕት ከ እንስት ጋር ሊገናኙ ዘር ይተኩ ዘንድ እና የህይወት ደስታን ያገኙ ዘንድ የመጀመሪያ የአብሮነት ማሰሪያ ገመድ ጋብቻ ይባላል። ጋብቻ ማለት በሰዎች መካከል የሚፈጠር የማህበራዊ አንድነት ስርዓት ወይም ህጋዊ ስምምነት ነው። ስርዓቱ የሚመሰረተው በሰርግ ስነ-ስረዓት ወይም በሌላ ዝግጅት ሊሆን ይችላል። እንደየ ባህሉ፣ እነደየ ሀይማቱ እና እንደየ ጊዚው ይለያያል። በወንድ እና በሴት መከከል ለሚፈፀም ጋብቻ ወንዱ ባል ሲባል ሴቷ ደግሞ ሚስት ትባላለች።

ሰዎች ጋብቻን የሚፈፅሙት በተለያዩ መንገድ እና አጋጣሚዎች ነው። ለምሳሌ ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋር ቅርብ የሆነ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሀይማኖታዊ እና ሌሎች መሰል ፍላጎቶችን በመገንባት እና የኖሩበትን ማህበረሰብ ወግ እና ልማድ፣ ባህል፣ ለመምሰል ሲሉ ጋብቻን ይፈፅማሉ። በሌላ በኩል የተለያዩ ወይም የተቃራኒ ጾታን ፍላጎት ለማርካተ አለመግባባትን ለማስቀረት ዘርን ለመተካት እና ሌሎች ተፈጥሯዊ ፍላጎቶችን ለሚሟላት ጋብቻን ይፈፅማሉ።

2.1.3.ቴአትር

ቴአትር የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ የሚያከናውናቸውን ድርጊቶች፣ ገጠመኞች አጠቃላይ የገሃዱን አለም እንቅስቃሴዎችን ቀንጭቦ እና አስውቦ ጥበባዊ መልክና ይዘት በማላበስ መድረክ ላይ ግልጥ አድርጎ የሚያሳይ የጥበብ ዘርፍ ነው። ይህ ዘርፍሲከወን ብዙሃን የጥበቡ ባለሙያዎችን ያሳትፋል። በዚህ ሀሳብ ላይ ሳሙኤል ተስፋዬ "የመድረክ ጀርባ ጥበባት" በተሰኘው መጽሐፍ እንዲህ ሲል ይገልፃል። «ቴአትር በርካታ ሙያተኞችን በአንድ ጥላ ስር የሚያሰባስብ ግዙፍ ጥበብ ነው።» [2010፤11] ሲል አብራርቶታል ይህም ዘርፈ ብዙ ጥበባትን ጠቢባንን እንደሚያሳትፍ የሚያሳይ ነው። ፋንታሁን እንግዳ ‹‹ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላትና ብያኔዎቻቸው›› በሚል መፅሀፋቸው ላይ እንደገለጹት። ‹‹... ተውኔት በማህበረሰቦች ወግና ባህል ተመስርቶ የሚመደረክ ባህላዊ ትርኢት ነው።›› (2001፤84)ይህም ተውኔት ወይም ቴአትር የእምነቶች፣ የክብረ- በአላት እና ስነ-ቃሎች የህዝቡ ልምዶች ላይ መሰረቱን ያደረገ ሲሆን እነዚህ ማህበረሰቦች ከሌሉ ሊኖር የማይችል ባህላዊ ትርኢት ነው። እንደ የሰርግ ትውፊት ያሉ ትውፊቶች ተፅፎ የተቀመጠ ፅሁፍ ባይኖረውም ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል እየተላለፈ የሚተገበር ክዋኔ ነው።

ሙዚቃዊ ተውኔት ከሌሎች የተውኔት ዘውጎች ጋር ሲነፃፀር የራሱ የሆነ መለያ ባህያት አሉት፡፡ይህም ከሌሎች የተውኔት ዘርፎች ልዩ ከሚያረገው ባህርያት መካከል፤ ፈንታሁን እንግዳ (2001፣85) ‹‹ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላትና ብያኔዎቻቸው›› በሚለው መፅሀፉ ውስጥ ባህርያቱን እንደሚከተለው ያስቀምጣቸዋል፡- “ትርኢቱ የሚቀርበው በመደበኛ ቤተ- ተውኔት ሳይሆን በገላጣ ስፍራ ነው፡፡ ፤ ትውፊታዊ ተውኔት በመዝሙር እና በውዝዋዜ ይታጀባል፡፡ ጥቅም ላይ የሚውሉ የመድረክ ቁሳቁሶች ባህላዊ ከበሮዎች ፣ ጭንብሎችና እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡“ በዚህ ሃሳብ ዉስጥ ሙዚቃዊ ተውኔት የሚታጀብበትን ከውዝዋዜ፤ከግብአተ ድምጽ፤ አልባሳትና ቁሳቁስ በነዚህና በሌሎችም የቴአትር ማሙያዎች ደምቆ የሚቀርብ የሰው ልጅ የተፈጥሮ ቅጅ ነው፡

2.1.5.ሙዚቃዊ ቴአትር

ሙዚቃዊ ቴአትር ሙዚቃን፣ውዝዋዜን፣ቃለተውኔትን እና ትወናን በዉስጡ አጣምሮ እና አዋህዶ በመድረክ የሚቀርብ አንዱ የቴአትር አይነት ነው፡፡በዘለማድ ሙዚቃዊ ቴአትር እንበል እንጅ ሙዚቃዊ ቴአትር ከሌሎች ቴአትር ዘውጎች ለየት የሚልበት የራሱ የሆነ ቅርጽ እና ይዘት አለው፡፡ *ዘሪሁን አስፋው፣ የስነ ጽሁፍ መሰረታውያን በሚል መጽሃፉ ተውኔትን እንዲህ ገልጸታል "ተውኔት የራሱ የሆነ ባህሪ ያለው ሲሆን አንዱ የስነ-ፅሁፍ ዘርፍ ነው፡፡ እንደሌሎች የስነ-ፅሁፍ ዘርፎች የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ ገፅታዎች ያንፀባርቃል፡፡" ፣ (2004፣ 261)* ሙዚቃዊ ተውኔት በዋናነት ሁለቱን የኪነ-ጥበብ ዘርፎችን ማለትም ሙዚቃ እና ተዉኔትትን የያዘ ነዉ፡፡ሙዚቃዊ ተዉኔት አጠቃላይ የሙዚቃዊ ቴአትር አላባዎችን የያዘ እና ሙሉ በሙሉ የሙዚቃዊ ቴአትር ባህርያትን በውስጡ ያቀፈ፤ ሙዚቃዊ ተውኔቶች ሴራን፣ ቃለተውኔትን፣ ገፀ-ባህሪን፣ ውዝዋዜን፣ ግጥምን፣ ዜማን፣ ድምጽንና የሙዚቃ መሳሪያን ይዞ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ ሙዚቃዊ ተዉኔት መላ የሙዚቃዊ ቴአትር ባህርያትን እና አላባዎችን እንገነዘባለን፡፡

2.2. ሙዚቃዊ ተውኔት አላባዎች

ሙዚቃዊ ተውኔት ሲፃፍ ተውኔቱን ወደፊት የሚያራምዱት የራሱ አላባዎች አሉት፡፡ እነዚህም የተውኔት አላባውያን የምንላቸው ናቸው፡፡ ጆን ኬንሪክ ፣ musical teatre hisyory በተሰኘው መጽሃፉ ላይ የሙዚቃዊ ተውኔት አላባውያንን በማለት አስቀምጧል፡፡ “ሙዚቃ፣ ሴራ፣ ውዝዋዜ ፣ ዝግጅት ፣ ቴክኒካል ግብአት ናቸው፡፡” (2008,15)[1] በማለት የተውኔት

አላባዎችን አስቀምጧል። የሙዚቃዊ ተውኔት አላባዎች በዋናነት ጭብጥ፣ ቃለ ተውኔት ፣ ሴራ፣ገፀ-ባህሪ፣ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ሲሆኑ ሙዚቃ ለሙዚቃዊ ተውኔት አቅርቦት መሠረታዊ ነገር ነዉ።የሙዚቃዊ ተውኔት አላባውያን ደግሞ ሙዚቃዊ ተውኔትን በእግሩ እንዲራመድ የሚያደርጉት መሰረታዊ ነገሮች ናቸው።

2.2.1. ሙዚቃ

ሙዚቃ የሰው ልጅ በህይወት ሲኖር ሀዘኑን፣ ደስታውን በአጠቃላይ የውስጥ ስሜቱን የሚያንፀባርቅበት አንዱ የጥበብ አይነት ነው። ሙዚቃ በተውኔት ውስጥ የሚኖረው ጣእም የሰመረ ይሆን ዘንድ ከሴራው ጋር የተያያዘ መሆን ይገባዋል።በሙዚቃዊ ተውኔት ውስጥ የሚገኝ ሙዚቃ ከሴራው ጋር በተጣጣመ መልኩ ሲዘጋጅ ይሁን ተብሎ አዲስ ሙዚቃ ሲዘጋጅለት ከሆነም ከዚህ በፊት ተደርሰው የነበሩ ሙዚቃዎች ሊቀናበሩበት ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ ጌታቸው በለጠ ፤የጥበባት ጉባኤበተሰኘው መጽሃፉ ላይ ስለሙዚቃ እንዲህ ሲል ገልጿል

> “ሙዚቃ ለስሜት ቅርብ ነው። በሙዚቃ ብዙ የህይወት ዘርፎችን መተርጎም ይቻላል። በተለይ በተውኔት ውስጥ ሙዚቃ ከገጸ ባህርያት ያልተናነሰ ሚና ያለው ተናጋሪ ጥበብ ነው። የተውኔት ሙኢቃ በአይነቱ ብዙ ነው። ገጸ-ባህሪው እራሱ ሊያንጎራጉር ይችላል። በመሳርያ የተቀናበሩ ሙዚቃዎችም አስፈላጊ ሆነው ሲገኙ በትእይንቶቹ መካከል ሊቀርቡ ይችላሉ። ሙዚቃ ለተውኔት ጥበብ ማጣፈጫ ቅመም ብቻ ሳይሆን እጅግ አስፈላጊ ግብአት ጭምር ነው።” [2004 ፤333]

በአጠቃላይ በሙዚቃዊ ተውኔት ውስጥ የድምፅ ግብዓቶች ፣ የተዋንያን ድምፅ ፣ ዘፈን በተውኔት ውስጥ ያሉ ስሜቶችን እያደመቁ ፣ የትዕይንቶች ድባብ እየመሰረቱና እያሻገሩ እንዲሁም በመሳሪያ ብቻ የተቀነባበሩ ሙዚቃዎችን በመጠቀም የሙዚቃዊ ተውኔቱን ሴራ ወደፊት በመግፋት ታሪኩን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማስፈንጠር ጥቅም ላይ ይውላሉ። በተውኔት ውስጥ ገፀ-ባህሪያት ፣ ህብረ ዘማሪያን የሚዘምሩት ዝማሬ የተውኔቱን ጊዜ ፣ የገፀ-ባህሪያትን ስሜት ፣ እንዲሁም ታሪኩ የሚፈፀምበትን ቦታ የመጠቆም አቅም አለው። በሙዚቃዊ ተውኔት ውስጥ ስለሚገኙ የዝማሬ አይነቶች ሳሙኤል ተስፋዬ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር የጥናት ምርምር ጆርናል" በሚል መፅሀፍ እንዲህ ሲል ያብራራዋል። የዝማሬ ወይም ዝማሬ በተውኔት ውስጥ ወደፊት ስለሚከሰተው ድባብ ማመላከት፣ ገፀ - ባህሪያቱን ማስተዋወቂያ

እንዲሁም የተውኔቱን ሙድ ማሳያ ነው። ሌላኛው ተራኪ ዘማሪዎች ሲሆን ይህ የዝማሬ አይነት ገፀ-ባህሪው በውስጡ ስለተሰማው ጥልቅ ስሜት ለተጋራው ገፀ - ባህርያት ወይም ለተመልካች የሚያጋባበት የዝማሬ አይነት ነው ሶስተኛው እና የመጨረሻው የመዝጊያ ሙዚቃ ሲሆን ይህ የዝማሬ አይነት ተውኔቱ አልባት ላይ መድረሱን፣ ሁሉም ድራማዊ ድርጊያዎች ማብቂያቸው ላይ መድረሳቸውን የሚያሳይ የዝማሬ አይነት ሲሆን በተውኔቶች አፈጻጸም ላይ ድምቀትን የሚፈጥሩ ናቸው።

ሙዚቃ ለሙዚቃዊ ተውኔት አንድ አላባ ከመሆኑም በተጨማሪ አብዛኛው ግዜ በመደበኛ ቴአትሮች ለትዕይንት መዚጊያ እና መክፈቻ፣ ለግብዓተ ድምፅ እና ለተለያዩ ስሜቶች መግለጫ ሆኖ ሲያገለግል ይታያል። ከዚህ ጋር ተያይዞ አያልነህ ሙላቱ "ደረጃ ሙዚቃዊ ድራማ" በተሰኘው መጽሐፉ እንዲህ ሲል ይገልጻል፦ ሙዚቃ የሰው ልጅ ስሜቱን የሚገልጥበት ረቂቅ መሣሪያ ነው።(19861፤68) ከጥቅሱ የምንረዳው ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ስሜታቸውን በሙዚቃ እንደሚገልጡ እና በሙዚቃዊ ተውኔት ዉሰጥ ሙዚቃ ሲሳል የተውኔቱን ታሪክ፣ ገፀ-ባህሪ፣ ጭብጥ እና አጠቃላይ ሀሳቡን እንድያገኝ ተደርጎ ይቀጻል።

2.2.2. ውዝዋዜ

ውዝዋዜ ለሙዚቃዊ ተውኔት አላባ በመሆን ለሙዚቃዊ ቴአትር ድምቀት እና ውበት የሚሰጥ ነው።በተጨማሪም ገፀ-ባህሪን ለመግለጥ እና ለታሪኩ ማጉላት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው።ውዝዋዜ በሁለት መንገድ ሊቀርብ ይችላል። በጋራ እና በግል የገፀ-ባህሪያትን ውስጣዊ ስሜት፣ ፍላጎታቸውን እና ሀሳባቸውን የሚገልጹት በውዝዋዜ ነው።ከሃሳቡ የምንረዳው ዉዝዋዜ በሙዚቃዊ ተውኔት ውሰጥ የገፀ-ባህርያትን እንቅስቃሴ፦ ግልፅ እና የተደበቁ አላማዎችን ለመግለጽ፣ ሀሳቦቻቸውን ገፀ-ባህርያት የሚገልጹበት እና ውሰጣዊ ስሜታቸውን ከጥግ እስከ ጥግ የሚገልጹበት ነው። አያልነህ ሙላቱ ፤ ደረጃ ሙዚቃዊ ድራማ በተሰኘው የቴአትር ጽሁፍ ላይ ስለ ውዝዋዜ እንዲህ በማለት ገልጿል። 'የሰው ልጅ ከጥንት ጀምሮ የመልእክት ስሜቱን ለመግለጽ ከተጠቀማቸው ዘዴዎች ዉስጥ አንዱ ውዝዋዜ ነው። ውዝዋዜ በድርሰት ሃሳብ ላይ ተመስርቶ በመድረክ ሲተረጎም መልእክት ይኖረዋል። አፍ አውጥቶ ይናገራል ፤ ያስተምራል።" [1986 ፤ 13] እንደተገለጸው ውዝዋዜ ገፀ-ባህሪያት የውስጣቸውን ስሜት ፈልጎ የሚያንፀባርቅበት እንቅስቃሴዎቹን የሚያደምቅበት ማስተላለፍ የተፈለገውን መልእክት በተገቢው ለማስተላለፍ እጅግ ድንቅ የሰውነት መሳርያ ነው።

2.2.3. መቼት

መቼትን በተውኔት ውስጥ መቼና የት ፣ ቦታንና ጊዜን የሚያሳይ አላባ ነው። በዘልማድ ተፈጥሮኣዊ እና ሰው ሰራሽ ብለን ልንከፍለው እንችላለን መቼት የአንድ ተውኔት ወይም ልብወለድ፣ የግጥም እና የፊልም ታርክ የሚከወንበት ቦታ እና ግዜ እንዲሁም ማህበራዊ

ሁኔታ የሚገለጥበት ነው። መቼት በስነጽሑፍ ሰራዎች ውስጥ ሙሉ የታርክን ማህበራዊ ሁኔታ እና ታሪኩ የት እና መቼ ተደረገ የሚሉ ጽንስ ሀሳቦችን ከዋናው ታሪክ ውስጥ እነዚህን ተሸክሞ ከታሪኩ ንችላለን።ከዚህ ጋር ተያይዞ ዘርሁን አስፋው "የስነ-ጽሑፍ መሠረታዊያን" በሚለው መጽሐፉ እንዲህ ሲል ያስቀምጣል፦የመቼት አይነቶች ከተውኔታዊ ቦታው አንፃር በአራት ይከፈላሉ። እነዚህም፦ የቤት ውስጥ መቼት፣ የቤት ውጭ መቼት፣ ባዶ መቼት እና ልዩ መቼት ናቸው።(1992፤79) መቼትን በዘልማድ በሁለት እንክፈል እንጂ ከተውኔታዊ ቦታው አንፃር በተለያዩ መንገዶች መክፈል እንችላለን ማንኛውም ተውኔት ስንጽፍ እነዚህን መቼቶችን መጠቀም እንችላለን ካልሆነ ግን ፈጽሞ የምናመጣው ታሪክ ሙሉ ሆኖ ሊገኝ አይችልም። የመከወኛ ቦታ ከዋኞቹ ትውፊታዊ ክዋኔዎችን ለተመልካች የሚከውኑበት ስፍራ ነው። ይህም ማለት በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥም ትልቅ ቦታ አለው። ተዋንያኑ ከተመልካቹ ተለይቶ የሚታይበት ሲሆን ይህም ቦታን ጊዜን እና ማህበራዊ ሁኔታን እንዲገልፅ ተደርጎ የተገነባ ነው።

በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ መከወኛ ቦታ መቼት የሚለውን የተውኔተ አላባ ይወክላል። መቼት የአንድ ተውኔት፣ ልብወለድ፣ የግጥም እና የፊልም ታሪክ የሚከወንበት ቦታ እና ጊዜ፣ ማህበራዊ እውነታን የያዘ ነው። መቼት "መች እና የት" የሚባሉትን ሁለት ቃላት የያዘ ሲሆን ትርጉሙም ተውኔታዊ ጊዜ እና የሚከወንበት ቦታን ያመለክታል። መቼት በምናብ ሊፈጠር የሚችል ወይም ደግሞ ትክክለኛ ትውፊቱየሚከወንበት ቦታ እና ጊዜን ያካተተ ሲሆን ይህም ለስረዓቱ ተብሎ የሚዘጋጅ ልዩ የሆነ ቦታ ነው። እናም ትውፊቱ የሚከወንበት ቦታ እና ወቅት የሚያንፀባርቅ ሲሆን ለትውፊቱ ተብለው በሚዘጋጁ ቦታዎች ላይ ይከወናል። በተጨማሪም ዘሪሁን አስፋው የስነፅሁፍ መሰረታውያን በሚለው መፅሀፍ ለይ እንዲህ ሲል ያስቀምጣል....

"መቼት ታሪኩ የተከናወነበት እና ገፀ-ባህሪያቱ የሚኖሩበት ወይም የኖሩበት

የገጠር ቦታ ወይመ የከተማ አከባቢ ብቻ አይደለም። አያሌ ነገሮችን ይጨምራል።

ከገጠሩ እና ከከተማው ህይወታዊ እንቅስቃሴ ጋረ ያሉትን የተለያዩ ሁኔታዎች አካቶ

በመያዙም ጓዘ ብዙ ነው።" 2004 ዓ. ም፣ 179

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ትውፊታዊ ክንወዋኔዎች በተወሰኑ ቦታዎች የሚከወኑ ናቸው። የመከወኛ ቦታዎችም እንደ ክንዋኔዎቹ የተወሰኑ ይሆናሉ። ይህም ማለት ቤተ-

ክርስቲያን፣ መስጊድ፣ወንዝ ላይ፣ ዋርካ ዛፍ ስር፣ በመኖሪያ ቤት ውስጥ ተብለው በተዘጋጁለት ቦታዎች ላይ ሊከወን ይችላል።

2.2.4. ገፀ-ባህሪ

ገፀ-ባህሪ የገሃዱ ዓለም ወኪል ሰዎች ሲሆኑ የተጻፈላቸውን ሀሳብ ነፍስ እንዲዘሩበት ህይዎት እንዲኖረው አድርገው ተላብሰው የሚጫወቱ የገሃዱ አለም ውክል ሰዎች ናቸዉ። "መሰረታዊ የተውኔት አጻጻፍ መርሆች"በሚለው መጽሐፍ ጫንያለው ወልደ ጊዮርጊስ፤ ተስፋዬ ገ/ማርያም፤አስታጥቃቸው ይሁን፤እቴነሽ ካሳ፤አለማየሁ ታደሰእ የጻፉት ሲሆን እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል። "የገጸ ባህሪ አሳሳል የምንለው አንዱ የተውኔት አጻጻፍ መርህ ሲሆን የሰውን ልጅ ባህሪያቶችን ገጽታ በተውኔት መስታወትነት የማቅረብ ቴክኒክን የሚያሳይ ነው።" [2001፤11] ይህም ሲሉ ገፀ-ባህሪያት የገሃዱን አለም ፍጡራን አምሳልና አካል ተለክተው የሚቀረጹ የልቦለድ፣ የተውኔት፣ የትረካ፣ የግጥም በጥቅሉ የፈጠራ ስራዎች ሰዎች ናቸዉ። ገጸ ባህርያት ማለት ተዋንያኑ የሚጫወቱት ድርሻ ነው። የሚና ክፍፍል በሙዚቃዊ ተውኔት ክንውኑ ውስጥ የድርጊት፣ የቃለ ምልልስ .... ወዘተ መሰል ድርጊቶችን ያካትታል። በከዋኞች መካከል ያሉ ክፍፍሎችን በውስጡ የያዘ ሲሆን ከዋኞች ያላቸውን የስራ ድርሻ የከዋኞች ሚናን በድርጊትም ሆነ በቃለ ምልልስ በትውፊት ውስጥ የሚወጡትን የድርሻ ሚና ይይዛል። ይህም ማለት ከዋኞች በሚከውኑት ክዋኔ ውስጥ ያላቸውን ወይም የሚወጡትን የስራ ድርሻ ወይም የድርጊት ክፍፍል ነው። በቃለ ምልልስ ከዋኞች በማህበረሰብ ተግባቦት በሰዓቱ እንደየ ሚናቸው የሚናገሩት ንግግር የሚና ክፍፍላቸውን ሊገልፅ ይችላል።

2.2.5.ሴራ

የሙዚቃዊ ተውኔት ታሪኩን እንደ መሰሶ በመሸከም ሴራው እንዴት መቅረብ እንደሚችል ሁኔታውን እና አካሄዱን የሚወስን ከዋነኞቹ አላባዎች አንዱ ነው። ሴራ በተውኔት ውስጥ በምክንያት እና በውጤት ወይም የግጭት እና የታሪክ ውጤት በመሆን ይፈጠራል። ሴራን በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴዎቻችን ልናገኝ እንችላለን። በሙዚቃዊ ተውኔት ውስጥ ሴራ ቃለተዉኔቱ፣ ሙዚቃን እና ዉዝዋዜን ለማስተሳሰር ታስቦ የተሰራ መሆን አለበት።በተውኔት ውስጥ ሴራ በሚጻፍበት ግዜ ለሙዚቃው እና ለውዝዋዜው መጣጣም እንዲኖረው ተደርገው

ይጻፋሉ። ጫንያለው ወልደጊዮርጊስ፤ተስፋዬ ገብረ ማርያም ፤አስታጥቃቸው ይሁን ፤ እቴነሽ ካሳ ፤ አለማየሁ ታደሰ በጻፉት “መሰረታዊ የተውኔት አጻጻፍ መርሆች” በጋራ በጻፉት መጽሃፍ ስለሴራ እንዲህ ብለው ገልጸውታል “የተስተካከለ የመጀመርያ ፤ መማከያ ወይም መካከለኛ እና መጨረሻ ክፍል ኖሮት በግልጽ እያደገ የሚሄድ መሆን አለበት”[2001፤112]

በዚህም መሰረት ሙዚቃዊ ተውኔቶች ሲሰሩ እንደ ቴአትር የተለያዩ የሴራ አይነቶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ ሴራ አልባ ተውኔቶች፤ልል ሴራ፤ጥብቅ ሴራን ሊጠቀም ይችላል። ሴራ ተውኔትን ወደፊት ለማራመድ ትልቅ ድርሻ አለው።

2.2.6.ጭብጥ

ጭብጥ ማለት የአንድ ስነ-ጽሑፍ ስራ ዋና ወይም ማዕከላዊ ሀሳብ ነዉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ ፋንታሁን እንግዳ "ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው" በተሰኘው መጽሐፉ እንዲህ በማለት ገልጾታል፦”ጭብጥ በስነ-ጽሑፍ ውስጥ ማለትም በተውኔት፤ በልብወለድ እና በግጥም ፈጠራዎች ውስጥ ማዕከላዊ ወይም ገዥ ሀሳብ የሚባለው ረቂቅ ሀሳብ ነው።” (1993፤ 112) ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ጭብጥ የስነ-ጽሁፍ ስራ ውስጥ ማስተላለፍ የተፈለገው አንኳር መልእክት ነው። “ ጫንያለው ወልደጊዮርጊስ፤ተስፋዬ ገብረ ማርያም ፣ አስታጥቃቸው ይሁን፣ እቴነሽ ካሳ፤አለማየሁ ታደሰ በጻፉት “መሰረታዊ የተውኔት አጻጻፍ መርሆች”መጽሃፍ እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል “ለህብረተሰቡ የሚያስተላልፈው ፍሬ ነገር ጠቃሚ የሆነ [ታሪካዊ፤ባህላዊ እውቀታዊ፤ ማህበረ ሰባዊ ፤ሁለንተናዊ...እሴቶችን ማንጸባረቁ ጭብጡ በደራሲው አስገዳጅነት የተጫነ ሳይሆን፤ከታሪኩና ከገጸ ባህርያቱ ተፈጥሯዊ እድገት ወይም ባህሪ የመነጨ መሆኑ” [2001፤114]

ስለዚህ ነው ጭብጥ ለአንድ ስነ-ጽሑፍ ስራ ጀርባ አጥንት ነው የሚባለው።ግጭት ገፀባህሪያት ከገቡበት የፍልምያ ማጥ ለመውጣት ሲታትሩ ሌላ ችግር ሲደርስባቸው እንደገና ለማርገብ ሲሞክሩ የሚታዩበት የልቦለድ አይነተኛ አላባ ነው።ግጭት በልቦለድ ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ሊቀረጽ ይችላል። ግጭት ገፀ-ባህሪያት ከራሳቸው፣ ከማሕበረሰቡ፣ ከተፈጥሮ እና ከሰው ጋር ሊሆን ይችላል ለአንድ ስነ-ጽሑፍ ታርክ ያለ ግጭት ሙሉ ታርክ ማምጣት አዳጋች መሆኑን እና ታሪኩ መሳጭ እንዲሆን ሁነኛ ሚና በመጫወት የጀርባ አጥንት መሆኑን ነዉ። ጭብጥ ማለት በተውኔት ውስጥ በተደራሲያን መተላለፍ የተፈለገው አንኳር መልዕክት ወይም ፍሬ ሀሳብ ነው። በተውኔት ውስጥ ጭብጥን ከቃለ-ተውኔት ፣ ከተውኔት ርዕስ ልናገኘው

እንችላለን። ጭብጥ ማለት መድረክ ላይ አንዴ ተመልክተን ስንወጣ ከተመለከትነው ተውኔት በእኛ ውስጥ የቀረው ሀሳብ ወይም በተውኔቱ አማካኝነት ተመልካች ጋር የደረሰው መልዕክት ነው። የጭብጥ ሀሳብ ሳሙኤል ተስፋዬ "የመድረክ ጀርባ ጥበባት " በሚል መፅሀፉ እንዲህ በማለት ያብራራዋል። ጭብጥ አንድ ፅሀፊ ተውኔት ድርሰቱን ሊፅፍ ሲነሳ ወይም ብዕርና ወረቀት ሲያዘጋጅ ለተመልካች ወይም ለተደራሲ ሊያስተላልፍ የፈለገው ዋና መልዕክት ወይም ፍልስፍና ነው። ጭብጥ የተውኔቱ አንኳር ሀሳብ እና የተውኔቱ መሰረት ነው። (2012 ፣187)

ጭብጥ በአንድ ተውኔት ውስጥ ከሚያስተላልፈው መልዕክት አንጻር በሁለት ይከፈላል። እነዚህም አካባቢያዊ ጭብጥ እና ሁለንተናዊ ጭብጥ ሲሆን ግለኛ ጭብጥ የምንለው ጊዜያዊ መልዕክት ያለው የጭብጥ አይነት ሲሆን ይህ አይነት ጭብጥ ያለው ተውኔት መልዕክቱን ተደራሽ የሚያደርገው በተወሰነ ጊዜና ለተወሰነ ማህበረሰብ ሲሆን እንዲህ አይነት ጭብጥ ያለው ተውኔት ከተፃፈበት ማህበረሰብ እና ጊዜ ውጪ ለተመልካች ሲቀርብ የሚያስተላልፈው መልዕክት ያን ያህል አይሆንም።

ሌላኛው ሁለንተናዊ ጭብጥ የምንለው የጭብጥ አይነት ሲሆን ይህ የጭብጥ አይነት ከስሙ እንደምንረዳው ሁሉን ያማከለ እና በማንኛውም ጊዜ ለተመልካች ወይም ለተደራሲያን ማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት የሚያስተላልፍ ነው።

2.2.7.አልባሳት

አልባሳት የቴአትር አላባ ሲሆን ተዋናዩ የሚለብሱት ልብስ ነው። በመደበኛው ቴአትር (ድራማ) የተወኔቱን ዘውግ፣ የተዋናዬቹን ምንነት የምንገልፅበት ነው። ከትውፊታዊ ድራማ አልባሳት የሚለየው ማንኛውንም አልባሳት ሊጠቀም ይችላል። ትውፊታዊ ተውኔት ግን አልባሳት እንደየማህበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ፣ባህልና ወግ የሚለያይ ነው። ከዋኞች ዝግጅታቸውን ጨርሰው ለህዝቡ በሚቀርቡበት ጊዜ የሚለብሱት ልብስ መጠሪያ ነው። ለምሳሌ፡- ጳጳሳት ፣ ቀሳውስት እና ዲያቆናት በክብረ- በአላትና ስርአት- ቅዳሴ ወደ ቤተመቅደስ በሚገቡ ጊዜ የሚለብሱትን ልብስና የሚዘረጉትን ጃንጥላ ይጨምራል። በዚህም ምክንያት አልባሳት ከቤተክርስቲያን ነው ይባላል። ይህንን አስመልክቶ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው በሚለው መፅሀፍ ላይ እንዲህ ሲል ያስቀምጣል::

" አልባሳት ተዋንያን ዝግጅታቸውን ለተመልካች በሚያቀርቡበት ጊዜ

የሚለብሱት ልብስ መጠሪያ ነው። አልባስ የሚለው ቃል ምንጩ

ከቤተ-ክርስቲያን ሲሆን ጳጳስ፣ ቀሳውስት እና ዲያቆናት በ ክብረ

በዓላት እንዲሁም ለስረዓተ ቅዳሴ ወደ ቤተ ክርስትያን በሚገቡበት

ጊዜ የሚለብሱት እና የሚዘረጉትን ጃንጥላ ይጨምራል። አልባሳት

ጊዜ እና ቦታን፣ የኑሮ ደረጃን፣ እምነትን፣ፆታን፣ የሙያ መስክን፣

የግላዊ ፀባይን እና የንቃተ ህሊና ደረጃን ሳይቀር ሊወክሉ

እና ሊያንፀባርቁ ይችላሉ።"/ፋንታሁን እንግዳ፣ [2001፣ 92]

በተጨማሪም አልባስ ትውፊታችንን የሚገልፅ መሆን አለበት ። ጊዜን ፣ቦታን፣ የኑሮ ደረጃን፣ እምነትን፣ ፆታን ፣የሙያ መለክን ፣ ግላዊ ፀባይንና የንቃተ ህሊና ደረጃ ሳይቀር ሊወክሉ ይችላሉ።

ለምሳሌ፦ አልባሳት ክፍለ ዘመንን ማወቅ እንችላለን። የኑሮ ደረጃን (ንጉስ፣ አሽከር፣ባላባት ወ.ዘተ) እናውቃለን።

2.2.8.ቃለ ተውኔት

ቃለ-ተውኔት ከተውኔት አላባዎች አንዱ ነው። ቃለ ተውኔት ሁለት እና ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው ገፀ-ባህሪያት በተውኔት ድርሰት ውስጥ እርስ በእርሳቸው የሚያወሩት የምልልስ ንግግር ሲሆን በልበወለድ፣ በግጥም፣ በመደበኛ እና በኢ-መደበኛ ወጎች ላይ አልፎ አልፎ ጥቅም ላይ ሲውል ይስተዋላል። ፋንታሁን እንግዳ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው በሚለው መፅሀፍ ላይ እንዲህ ሲል ይገልፃል " ቃለ ምልልስ ሁለት እና ከዚያ በላይ ገፀ-ባህሪያት በተውኔት ድርጊት ውስጥ እርስ በእርሳቸው የሚያደርጉት የምልልስ ንግግር ሲሆንበልብወለድ በግጥም፣ በመደበኛ እና በኢ- መደበኛ ወጎች ላይም አልፎ አልፎ ጥቅም ላይ ሲውል ይስተዋላል።"/ፋንታሁን እንግዳ፣[2001፣62]

ቃለ ተውኔት በአንድ ተዉኔት ውስጥ ከገፀ ባህሪያት አንደበት የሚወጣ ቃል ነው። ፤ ቃለ ተውኔት በተውኔት ውስጥ ገፀ ባህሪያት ማንነታቸውን ለማሳወቅ፣ ከሌላ ገፀ ባህሪያት ጋር ለመግባባት ይጠቀመበታል።ፋንታሁን እንግዳ "የተዉኔት አጻጻፍ ዘዴ" በሚለው መጽሃፉ በገፀ ባህሪያት መካከል የሚደረግ የቃል ልዉዉጥ እንዲህ ሲል ያብራራዋል። "ገጸ ባህርያት የሚጠቀሙት ቃለ ተውኔት እንደ ተውኔቱ ዘውግ ሊለያይ እና የተውኔቱን አይነት ያማከለ ሊሆን ይችላል። ይህም በትራጀዲ የተውኔት አይነት ውስጥ ገፀ ባህሪያት የሚጠቀሙት ቃለ-

ተውኔት ጠጠር ያለ እና ውስጠ ወይራ ያለው ሲሆን በኮሜዲ ተዉኔት ላይ ደግሞ ገፀ ባህሪያት የሚጠቀሟቸው ቃለ ተውኔቶች ቀለል ያሉ እና ውስብስብ ያልሆኑትን ነው። በተጨማሪም ገፀ ባህሪያት መሀከል የሚደረግ ምልልስ ወይም ቃለ-ተውኔት መቼትን ለመግለፅ ፣ ገፀ ባህሪያትን ለማስተዋወቅ፣ ታሪክን ለመንገር እንዲሁም ሴራን ወደፊት ለማራመድ ስራ ላይ ይውላል።

በተውኔት ውስጥ ቃለ ምልልስ በዝርው፣ በግጥም እና በዜማ ልናገኘው እንችላለን። ይህም የሚወሰነው የትውፊቱን ባለቤት የሆነውን ማህበረሰብ እንደሚጠቀምበት ሁኔታ የተወሰነ የሚሆን ነው። በመዝሏዊ ተውኔት ውስጥ ግን በግጥማዊ ይዘቱ ሰፊውን ድርሻ ይይዛል።

2.2.9.ቁሳቁስ

በትውፊታዊ በተውኔት ውስጥ ቁሳቁስ ማለት ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸው የሚፈጠሩ ሳይሆኑ ያሉና የሚኖሩ ቁሳቁሶችን ማህበረሰቡ ለትውፊቱ ሲል የሚጠቀምባቸው ናቸው። ቁሳቁስን ሳሙኤል ተስፋየ እንዲህ ይገልጸዋል

> “ቁሳቁስ በመድረክ ላይ የምንጠቀምባቸው ቁሳቁሶች በሙሉ የሚጠሩበት ስያሜ ነው። ከነዚህውስጥ ተዋንያን በእጅ የሚይዟቸው ትንንሽ እቃዎች ለምሳሌ፤ የሻይ ብርጭቆ፣ ሲኒ፣ደብዳቤዎች ፣ መጻህፍት፣ ከረሜላዎች ፣ ሻማዎች ወዘት ይጠቀማሉ (hand props)። ሌላኛው ግላዊ ቁሳቁስ(personal props) የሚባለው ሲሆን አንድ ተዋናይ ለግሉ የሚጠቀሙባቸውእቃዎችን ብቻ ይመለከታል። ለምሳሌየእጅ ሰአት፣ የሲጋራ ፓኮ፣ ሞባይል ስልክ፣ ጌጣጌጦች ሊሆኑ ይችላሉ።” (የትወና ጥበብ፣ 2010፣ 48)

ይህም ከዋኞች የሚጠቀሙባቸው ማንኛውንም ለትውፊቱ መከወኛ ወይም ትውፊቱን ለማከናወን የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች ሲሆን ቁሳቁሶቹም ባህላዊ የሆኑ መሆናቸወን ያስረዳል፡ ፡ በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸው የሚፈጠሩ ሳይሆን ያሉ እና የሚኖሩ፣ ቁሳቁሶችን ማህበረሰቡ ለትውፊት ሲል የሚጠቀምባቸው ናቸው። ቁሳቁስ ማለት በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ ከዋኞች የሚጠቀሙባቸው ማንኛውም አይነት እቃዎች ናቸው። በቁሳቁስ ከዋኞች በክንዋኔው ውስጥ ያላቸውን ሚና እና ማንነታቸውን በቀላሉ ለተመልካች ሆነ ለተሳታፊው ሊያሳውቃቸው ወይም ሊያስረዳቸው ይችላል። ይህም ከዋኞች የሚጠቀሙባቸው

ማንኛውም ለትውፊት መከወኛ ወይም ትውፊትን ለማከናወን የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች ሲሆኑ ቁሳቁሶቹም ባህለዊ መሆናቸውን ያስረዳል

2.3. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

አጥኚው ይሄን ጥናታዊ ጽሑፍ በሚሰራበት ግዜ ከጥናቱ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ጥናታዊ ጽሑፎችን ቃኝቷል። በመሆኑም አጥኚው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተመሳሳይነት አላቸው ያለውን ጥናታዊ ጽሑፎችን አስፍሯል።

2010ዓ.ም በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በደራርቱ ከበደ "ሆድ ባሰን መዚቃዊ ቴአትር ከመዚቃዊ ቴአትር እሳቤ አንጻር" ጥናቱ መዚቃዊ ቴአትር ባህርያትን ሙሉ በሙሉ በመተንተኑ፤ ከመዚቃ ፣ ከውዝወዜ ፣ ከጭብጥ እንዲሁም ከሴራ አንፃር በመተንተኑ ያመሳስላቸዋል ። በተጨማሪም ሁለቱም ጥናቶች የተሰሩት ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲና በቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርትስ ኦፍ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ መሆናቸው ያመሳስላቸዋል። ጥናታዊ ጽሑፉ የተሰራው ትውፊት ላይ ባለ መሆኑ እና ጥናቱ የሚያተኩረው በመዚቃዊ ቴአትር እሳቤ አንፃር ሆድ ባሰን መዚቃዊ ቴአትርን የተሰኘው ቴአትር በመተንተኑ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ የሶዶ ጉራጌ ማህበረሰብ ትውፊታዊ የሰርግ ስርአት ላይ መሆኑ የተለያዩ ያደርጋቸዋል።

ፋንታነሽ አበራ2008 ዓ.ም በዎሎ ዩኒቨርሲቲ “የራያ ቆቦ የሰርግ ስነ-ስርዓት ከትዉፊታዊ ተዉኔት አንፃር” ሁለቱም ጥናታዊ ፅሁፎች በየባህላቸው ስርአት ባለዉ መልኩ የሰርግ ስነ-ስርዓትን ተንትነዉ፤ በመቀጠልም በሰርግ ስነ-ስርዓት ላይ የተሰሩ መሆናቸውና ፣ለተመሳሳይ ዓላማ ብሎም ለመመረቂያ ፅሁፍ መዋላቸዉ::በሁለቱ ጥናቶች መካከል ያለዉ ልዩነት የቦታ፤ የቋንቋ ፤የባህል፣ የሰርግ ሰርአት ልዩነት የኑሮ ዘይቤ ልዩነት ያላቸው ሲሆን በአማራ ክልል ዉስጥ የራያ ቆቦ የሰርግ ስነ-ስርዓት ጎጃም ውስጥ ባለ ባህል ላይ የተሰራ ሲሆን፤ ይህ ጥናት ከደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በሶዶ ወረዳ የክስታኔ ማህበረሰብ ስርአት ውስጥ የተሰራ ነው፡ በመካከላቸውም ከላይ የተጠቀሱት ልዩነቶች አሏቸው።

ምዕራፍ ሶስት

3.የመረጃ ትንተና

3.1.የጉራጌ ማህበረ ሰብ ታሪካዊ አመጣጥ

የ“ጉራጌ” አመጣጥና ስያሜን በተመለከተ በርካታ ጥናቶች እንደሚያረጋግጡት በአመዛኙ ጉራ እና ጌ ከተባሉት ሁለት ቃላት ተዋቅሮ የመጣና መገልገያ ስያሜ እንደነበር ከ1332 ዓ.ም እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በዘመነ ንጉስ አምድፅዮን ጀምሮ መገልገያ ስያሜ እንደ ነበር ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ የአዝማች ስብኃትና ተከታዮቻቸው አይመለልን የግዛቱ መቀመጫ ማዕከል አድርገው ቆይተዋል፡፡ ስለ ጉራጌ ብሄረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ ቁርጥ ያለ አሳብ ባይሰነድለትም የተለያዩ ምሁራንና አፈ ታሪኮች የተለያዩ እሳቤዎቻቸውን አስቀምጠዋል፡፡ ስለ ብሄረሰቡ ታሪካዊ አመጣጥ መንግስቱ ሃይለማርያም፣ፍቅሬ ሃይለማርያም፣ተስፋዬ መኩርያ፣ ተዘራች ቢረዳ፣ግርማ ጥላሁን፣ ምትኩ ተሾመ በጋራ ሆነው በጻፉት “ጎጎት የጉራጌ ብሄረሰብ ታሪክ በሚለው መጽሃፍ ላይ እንዲህ አትተዋል፡፡

> “የጉራጌ ህዝብ ታሪካዊ አመጣጥን በተመለከተ የተሰነዘሩት አሳቦችም ሆኑ የተደረጉት ጥናቶች አብዛኞቹ መሰረት የሚያደርጉት ጉራጌ በአጼ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግስት (1314-1344)በሰሜን አኢትዮጵያ ጉራዕ ከተባለው ስፍራ በአዝማች ስብሃት መሪነት መጥቶ አይመለል ከተባለው አካባቢ የሰፈረ ሰራዊት እንደነበር ከሚነገረው ታሪክ ላይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የታሪክ ጽሃፍት ጉራጌ የሚለው ስያሜ የመጣው ጉራዕ ከተባለ ስፍራ የተወሰደ እንደሆነና ከአዝማች ስብሃት መምጣት በኋላ የተገኘ መጠርያ መሆኑን በማስረዳት ትርጉሙን ይተነትናሉ፡፡”

ከላይ እንደገለጹትም ከአዝማች ስብሃትና ተከታዮቻቸው ከጉርአ ተነስተው ለ400 ዓመት ከሰሜኑ አስተዳደር ተነጥሎ የቆየውን የቀድሞ የሰሜን መንግስት አካል የነበረውን የጉራጌ አካባቢ የሰሜኑ መንግስት መልሶ ከተቋቋመ በኋላ ተመልሶ የማዕከላዊ ግዛት አካል ሆኗል፡፡ ስያሜውም የጉርአ ሰዎች ሃገር ከሚለው የተወሰደ ሲሆን የህዝብና የአካባቢው ስም መጠሪያ ሆኖ እንዲቀጥል የንጉሱ ፍቃድና ዕውቅና እሳቸው ወደ አካባቢው ያቀላቀሏቸውን ሰዎች መነሻ ማድረጉ ይታመናል፡፡ ስለ ስያሜው ያካባቢው ተወላጅ የጉራጌ ዞን የሶዶ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ አቶ ጸጋዘአብ አለማየሁ፡፡

እንዲህ ብለዋል " "ጉራ" የሚለው ስያሜ የሰው ስም ሲሆን "ጌ" ማለት ደግሞ ቤት ማለት ነው። የጉራጌ ጥቅል መጠርያው የጉራ ቤት ማለት ነው ይባላል።" የብሄሩ መጠርያ አሬም ድረስብ ጉራጌ ተብሎ ይጠራል።

3.1.1. የህዝብ አሰፋፈር እና መልከዓ ምድር

በአለም የኋላ ታሪክ ውስጥ እየሰራ ባለውና በሰፊው ተቀባይነት ያለው የህዝብ አመጣጥና አሰፋፈር ታሪክ ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ምድር መሆኗን የሚያረጋግጥ ነው። "የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪው ሃሮልድ ጂ. ማርከር የጻፈው እና በሙሉቀን ታሪኩ የተተረጎመው የኢትዮጵያ ታሪክ የተሰኘው መጽሃፍ "ከሰው ልጅ መገኛዋ ሀገር የተነሱት እና በመላው አለም የተሰራጩት ህዝቦች መሀከልበሂደት ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች ተመልሰው ወደ እናት ምድራቸው ከደቡብ አረቢያ ተነስተው በዳህላክ ደሴቶች በኩል የገቡ ሲሆን ከነባሮቹ ኩሻዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር በአንድነት በሰሜኑ የሀገሪቱ አካባቢ ኖሩ" ሲል ያስረዳል። [1995 ፤ 21]

በሂደትም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመንቀሳቀስ የዛሬ ይዞታቸውን እንዳነፀ ይታመናል። በደቡብ አቅጣጫም በኤደን፣ በዘይላና በርበራ በኩል የገቡና በተለያዩ አካባቢ ሰፍረው እንደሚገኙም ይታወቃል። ይህም ውጤት ማለትም የነባሩ የኩሽ እና የሴማውያኑ ትስስር የአክሱም ጠንካራ መንግስትን፣ የአክሱማውያን ህዝቦችን እና ታላቁን የአለማችንን ቀደምት ስልጣኔ ማስገኘቱን ከላይ የተጠቀሱት ጸሀፊ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ በመጽሀፎቻቸው አትተዋል።

የጉራጌ ህዝብ ሰፍሮበት የነበረው መልከአ ምድር እና ህዝቡም የነባሩ የኩሻዊ ቋንቋ ተናጋሪ እና የሴማዊያኑ የቋንቋና ባህል ውርርስ ተዛምዶ ውጤት ነው። ይህ አካባቢም የአክሱም መንግስት ወታደራዊ መስፋፋት ያስገኘው ውጤት ነው። የጥንት ግዛት ወሰን ድንበር በዋነኝነት በወንዞች፣ በሀይቅ፣ በተራሮች፣ በደን፣ በገደላገደል በአጠቃላይ በተፈጥሮ አካል ይካለሉ ነበር።

በታሪክ የጉራጌ ህዝብ የሰፈረበት ምድር በሰሜን ምስራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የአዋሽ ወንዝ፣ በደቡብ ምዕራብ የጊቤ ወንዝ፣ በደቡብ ከሃድያ እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ ከዝዋይ ሀይቅ ጋር እንደሚዋሰን ይታመናል። በአሁን ወቅት ይህ ቦታ ከጉራጌ በተጨማሪ የኦሮሞ፣ የስልጤ፣ የሀላባ፣ የማረቆ እና የቀቤና ማንነትን ይዘው ያሉ ብሔረሰቦች መልከአ ምድር ነው።

3.1.2. በቤተ ጉራጌ የሶዶ ክስታኔ ብሔረ-ሰብ

አጥኝው ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ እንዳልካቸው ግዛው ጋር በቃለ ምልልስ በነበረው ቆይታ ስለሶዶ ክስታኔ እንዲህ ብለዋል።

> “የክስታኔ ብሄረሰብ በቤተ ጉራጌ ማኅበረሰቦች ውስጥ አንዱ ሲሆን ሶዶ ጉራጌ እየተባለም ይጠራል። በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በቀድሞው አጠራር በሸዋ ክፍለ ሃገር በአሁኑ በጉራጌ ዞን በሶዶ ወረዳ የሚገኝ ማህበረሰብ ነው። ክስታኔ፣ በመባል በወል ከሚጠሩት የቤተ ጉራጌ ማህበረሰቦች ውስጥ አንዱ ነው። የክስታኔ ህዝብ ቋንቋ ክስታኒኛ ይባላል። ክስታኒኛ የደቡባዊ ኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋዎች አካል ሲሆን የሶዶ ክስታኔ ተወላጆች መነጋገርያ (መግባቢያ) ቋንቋ ነው።” በማለት አብራርተዋል።

የክስታኔ ተወላጆች በብዛት በጉራጌ ዞን በሶዶ ወረዳ የሚገኙ ሲሆን እንዲሁም በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍለ ሃገራት ይኖራሉ። በማህበረሰቡ ዉስጥም በርካታ ባህሎች ይገኛሉ ለምሳሌ አዳብና፤ሸባል ወይም ሰርግ፤የለቅሶ ስርአት፤ግቦ፤ኬርታ፤ አንቃት[የገና ጨዋታ እና ሌሎችም ይካተቱበታል። ከነዚህ ትውፊቶች መካከል አጥኚው የሚዳሥሰው የሸባል [ሰርግ ስርአትን ነው።

3.2. ባህላዊ ሸባል [ሰርግ] በክስታኔ

ከጥንት ጀምሮ ለአቅመ አዳም በደረሰ ወንድና ለአቅመ ሄዋን የደረሱ ሴት ልጆች ጥንዶች በጋራ ለመኖር የጥምረት ትእይንት ነው። የጋብቻ ሥነ ስርዓት ወይም ሠርግ የሠዎች የጋብቻ ሥርዓት እንደየ ባሕሉ እና ወጉ ይለያያል። ባህላዊ ወይንም በሌላ ተመሣሣይ ሥርዓት ውስጥ ለመተሳሰር ቃል የሚገቡበት ዝግጅት ነው። ሰርግ በሁሉም አለም በሰው ልጆች ሂዎት ውስጥ የሚከወን የደስታ ጊዜ ነው። ሰዎች ይጋባሉ ይህንኑ ለትውልድ ያስተላልፋሉ ።ይህም በቤተ ጉራጌ በሶዶ ክስታኔ ብሄረሰብ ሸባል ተብሎ ይጠራል። በመጀመርያ የሚካሄደው እጮኝነት ነው። ይህም በሁለት አይነት መንገድ ይካሄዳል

1ኛ ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ሲደርስ አይቶ የወደዳትን ለናት አባቱ በመንገር እንዲታጭለት የሚጠይቅበት

2ኛ የወንዱ ልጅ ቤተሰቦች ወይም ወላጆች ለልጃቸው ትሆናለች የሚሏትን መርጦ ማጨት ናቸው።

በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ የሰርግ ስርአቱ የሚጀምረው ከዚህ ጊዜ አንስቶ ነው። ወንዱ ባህሉ በሚፈቅደው መልኩ አይኑ የወደዳትን ወይም ቤተሰቦቹ የወደዷትን ልጃገረድ ቤተሰቦቹ እንዲጠይቁ አክብሮ ሽማግሌ ከላከና እሺታን ካገኘ የሰርጉ ስርአት ዝግጅት ይጀምራል።የሰርጉ መጀመርያ የሚሆነውም ቸግ ተብሎ ይታወቃል።

3.2.1. ቸግ

ቸግ የልጂቱ ቤተሰቦች እሺታቸውን ካሳውቁ በኋላ የሚደረግ ክንውን ነው።በእለቱም የልጂቱ ቤተሰቦች ወዳጅ ዘመዳቸውን ያካባቢውን፤ማህበረሰብ፤ ጎረቤት ጠርተው ያሳድማሉ። ታላቅ ድግስ ደግሰው ከወንዱ ቤተሰብ የሚመጡትን ቤተዘመድና ሽማግሌዎችን በአክብሮት ይቀበላሉ። የወንዱ ቤተሰብም ለልጂቱ የሚሆኑ ሙሉ ጌጥ ይዘው ብሎም ያንገት፤ የጣትና የጆሮ ጌጦችን እንዲሁም የተለያዩ ልብስና ጫማዎችንና የእጅ ገንዘብ በማቅረብ ተመራርቀው የሰርግ ቀን ጥለው የአካባቢው ውጣቶችና ማህበረሰብ በጭፈራ በጨዋታ አድምቀው በአንድ ቀን ውሎ ስርአቱ ይጠናቀቃል። ይህ ስርአት የሚከወነው ከሰርጉ ቀን ቢያንስ ከአንድ አመት ቀደም ብሎና ከዛም በላይ ሲሆን እስከ ሰርጉ እለት ድረስ በሁለቱም እጮኞች ቤት ጨዋታ ጭፈራና ድግሶች ይኖራሉ ሆኖም ግን ሁለቱ እጮኞች ተጋብተው አብረው እስኪኖሩ ድረስ አይን ለአይን መተያየትም ሆነ መገናኘት ነወር ነው።

3.2.2.በቸግ ቀን የሚደረጉ ጨዋታዎች

ወንድና ሴት ሆነው የሙሽሮች ጓደኞች ጠላ እየጠጡ የተደገሰውን ድግስ በልተው የሙሽራውን ደስታ ተሰብስበው በጨዋታ ይገልጻሉ ጨዋታዎቹም በአማርኛና በክስታኔኛ ቋንቋ ይጫወቱታል ይህም የሆነው አብዛኛውን የክስታኔ ማህበረሰብ የአማርኛ ቋንቋን አጥርተው መቻላቸው ነው።

> “አውጪው ፡ ወይዘሪት ሙሽሪት እድልኛ ነሺ ከስላሴ ደብር አንዱን አገኘሺ ወንድ ተቀባዮች፡አዎኦ አዎኦ አዎኦ ሴት ተቀባዮች፡እዌዌ እዌዌ እዌዌ እዌዌ ላውጪ፡ እዲ ተደሽ ፈያ ይታኛ ንጮኙ አኻርሽም ዜግነት ትግላሜጭኙ ዬምጣ ደንገኛነት ትስላሜጭኙ ትርጉም፡ እኔም አንቺም ዉብ ነን አንበላለጥምበኪሴ መቀደድ ብትገለምጪኝም ኪሴ የተሰፋ እለት መምጣትሽ አይቀርም” በዚህ መልክ የሚቀርበው ጨዋታ ሁለቱ ሙሽሮች በመገናኘታቸው የደስታቸውን ስሜት የሚገልጹበት ነው።

3.2.3. ጥፍር ቀፈፋ

ጎጂ የሆነው የጥፍር ቀፈፋ እየቀረ ቢመጣም ባህሉ ግን እንዳለ ነው። በጥፍር ቀፈፋ ወቅት ልጂቱ ከቤት መውጣት ታቆምና በቅርብ ዘመዷ ቤት ጥፍሯን ትቅፈፋለች።ልጅም

በተመሳሳይ በየዘመዶቹ ቤት እየተሟሟረ ለሙሽርነት ይዘጋጃሉ በዚህ ወቅት ሙሽሮች እንደመሆናቸው መጠን ስራ እንዲሰሩ አይፈቀድላቸውም የሚመገቡት ምግብም ከወትሮ የተለየ ይሆናል።በነዚህ ጊዜያት ሙሽሮቹ በተገኙበት ሁሉ ጨዋታ ይደራል። በተለይ የኩዳዴ ጾም ከተፈታበት ጊዜ አንስቶ ሰፈር መንደሩ ሁሉ በጨዋታ በጭፈራ ይደምቃል። “ጥፍር ቀፈፋ የተፈለገበት ምክንያትም ሙሽሪቱ በወሲብ ወቅት በጥፍሯ ሙሽራውን እንዳትቧጭረውና እንዳታሸንፈው የታሰበ ነው።” ብለዋል። በሶዶ ጉራጌ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አላፊ እንዳልካቸው ግዛው። በዚህ ወቅት ሌሎች የሙሽሪት ጓደኞችና የቅርብ ቤተሰቦቿ እኩዮቿ አብረው በመሆን

የደስታዋ ተካፋይ ይሆናሉ።

3.2.4. የእንጨት ፈለጣ ቀን

ሰርጉ ከመድረሱ አንድ ወር ቀደም ብሎ የሚከወን ሲሆን የአካባቢው ማህበረሰብ በተለይ ወጣቶች ተሰባስበው የሰርጉ ድግስ የሚከወንበትን እንጨት ሲፈልጡ ይውላሉ።በተመሳሳይ በሴቶች በኩል የሰርጉን እህል ማስፈጨት።እቃ መዋዋስ እና አስፈላጊውን ዝግጅት ያደርጋሉ። ሲመሽ የደራ ጨዋታ ይካሄዳል። ከዚህ ጊዜ በኋላ የሰርግ ዝግጅቱ እየጠነከረ ይመጣል የሰርግ ደብዳቤዎችም ይበተናሉ።የሚካሄደው የጨዋታ አይነት ጎሮሮ ሲሆን በዚህ መልኩ ይጫወቱታል

ሸባልደ ሰላልኮ እንጨደ ፈለጡት

ውርሰንበት መሸማን ሙሽራደ ያመጣት

ትርጉም፡ ሰርግህ ደረሰና እንጨት ተፈለጠ

የሙሽራህ መምጫ ቀኑ ደረሰልህ እየፈረጠጠ

አውጪ፡ ይበሎ ጎይ ፈያ ጉንስና ቃይሳ

ይረግጥ ጎይ ፈያ ቀንዥር ተጉልማሳ

ተቀባዮች፡ እው ኤ እውኤ እውኤ

ትርጉም ፡ቆሙን በአይብ አጥቅሰው ሲበሉት ይጥማል

ወንድ ከሴት ጋራ ሲጨፍሩ ያምራል

በክስታኔ ማህበረሰብ የሃገር ሽማግሌ የሆኑት አቶ አለሙ ገቢ “በእንደዚህ ሁኔታ በሚከወንበት ወቅት ሌሎች ለአቅመ አዳም የደርሱ እኩያሞች ተያይተው እርስ በርስ ሊተጫጨበት የሚችሉበት ሁኔታም አንዳንዴ ሊፈጠር ይችላል” የሃገር ሽማግሌው እንዳሉትም አንድወጣት የፈለጋትን ሴት ልጅ የሚያይበት ነው

3.2.5. የጌሾ ወቀጣ ቀን

የጌሾ ወቀጣ ሰርጉ አስራ አምስት ቀናት ሲቀሩት የሚከውን ሲሆን ለጠላ ዝግጅት ያአካባቢው ማህበረሰብ ተሰባስቦ ጌሾ ወቀጣ ስርአቱን በጋራ ይፈጽማሉ። በእለቱም ድል ያለ ድግስ ይደገሳል። በእንጨት ፈለጣ ቀን የተጫወቱት የደራ ጨዋታ ይካሄዳል። በእነዚህ ጨዋታዎች ዉስጥ ቃለተውኔቶቹ ሙሉ ለሙሉ ግጥማዊ ሲሆኑ የሚጫወቱት ደግሞ በዜማ ነው። ይህም የሙዚቃዊ ተውኔት ባህሪን የተላበሰ ይዘት አለው። በክስታኔ ማህበረሰብ የሃገር ሽማግሌ የሆኑት አቶ አለሙ ገቢ ስለጌሾ ወቀጣ ቀንም እንዲህ ብለዋል። “ብዙዎቹ ሂደቶች ላይ የሚከወኑት ክውኖች ላይ ተመሳሳይ የሆኑ ተግባራት ናቸው። እንደ እንጨት ፈለጣ ቀን ሁሉ ጎረቤት ወዳጅ ዘመድ ሁሉ ተሰባስበው ደግሰው ጌሾውን በጋራ ይወቅጡታል። ጌሾው ደግሞ አስፈላጊነቱ ለሰርጉ ቀን ጠላ መጥመቅያ ነው።”

3.2.6.የኮሶ ቀን

የኮሶ ቀን ሰርጉ ሶስት ቀናት ሲቀሩት የሚከወን ስርአት ሲሆን የሚካሄደውም በሴት ሙሽራዋ ቤት ብቻ ነው። “ኮሶ አሁን አሁን እየቀረ የመጣ ባህል ነው ከጥቂት አመታት በፊት እጅግ በጣም ጎጂ ባህል ነበር በርግጥ አሁንም አልፎ አልፎ ይታያል።” ብለዋል የአካባቢው ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ መርከብ አለማየሁ። ባህሉም ኮሶ ተወቅጦ ከተዘጋጀ በሁዋላ የሙሽሪቱ ወዳጆችና እኩዮች ሁሉ አብረዋት ይጠጣሉ።አብረዋት ለጠጡት ሁሉ ልዩ ድግስ ይዘጋጃል ብሎም ኮሶ በጠጡት ሰዎች ስም ይታረዳል የጉራጌ ክትፎ ተሰርቶ ይቀርብላቸዋል። እስከ ሰርጉ እለት ልዩ ድግስ ይቀርብላቸዋል።የኮሶው ጥቅም ደግሞ ሙሽሪቱ በወሲብ ወቅት ሙሽራው በቀላሉ እንዲያሸንፋት ለማድከም የሚጠቀሙት ነው። ብለዋል አዝማች አለሙ ገቢ በሶዶ ጉራጌ ያካባቢ ሽማግሌ

3.2.7. የእንሾሽላ ቀን

የጉራጌ ተወላጅ የሆኑት ወይዘሮ ሸዋዬ ስለ እንሾሽላ እንዲህ ብለዋል እንሾሽላ ሰርጉ ሁለት ቀን ሲቀረው ብሎም ሰርጉ እሁድ ቀን ሲሆን አርብለት ምሽት በየሙሽሮቹ ቤት የሚደረግ ስርአት ነው። በእለቱም ወዳጅ ዘመድ ጎረቤት ተሰብስቦ ሙሽራውን እየመረቁ

እየተጫወቱ እየጨፈሩ ዉለው የሚያድሩበት ስርአት ነው።በንሾሽላ ቀንም የሚካሄዱ ጨዋታዎች እኒህ ናቸው። በማህበረሰቡ ውስጥ ነዋሪ የሆኑት መርከብ አለማየሁ ስለ እንሾሽለ እንዲህ ብለዋል። “እንሾሽላ አርብ እለት ማታ የሚከወን ሲሆን ወዳጅ ዘመድ ተሰባስቦ ሙሽሮችን በመመረቅና በመጨዋወት የሚከወን ውፊት ነው።” ከላይ እንዳሉትም ጨዋታው በዚህ መልኩ ይከወናል።

አውጪ፡ እንሾሽላ ያግድልከ ጎይ ያቦ ያዮ በለ

ተቀባዮች፡ እንሾሽላ ያግድልከጎይ ያቦ ያዮ በለ

አውጭ፡ እንሾሽላ ያግድልከጎይ ያቢዲ ነው በለ

ተቀባዮች፡ እንሾሽላ ያግድልከጎይ ያቦ ያዮ በለ

አውጭ፡ እንሾሽላ ያግድልከጎይ ይሚትዲ በለ

ተቀባዮች፡ እንሾሽላ ያግድልከጎይ ያቦ ያዮ በለ

አውጭ፡ እንሾሽላ ያግድልከጎ የኢትዮጵያ በለ

ተቀባዮች፡ እንሾሽላ ያግድልከጎይ ያቦ ያዮ በለ

አውጭ፡ እንሾሽላ ያግድልከጎ ጉራጌ ነው በለ

ሰለለለለለለለለለል

እልልልልልልልልልልል

አውጪ፡ የወሬ የወሬ ነጎ ጎሽ

ተቀባዮች፡ እህ

አውጪ፡ውሬሪ እለፊ እለፊ

ተቀባዮች፡ እህ

አውጪ፡በሰብ ይን ትረፊ

እልልልልልልልልልልል

ጎሮ እወኤ....

የሚጠቀሙት የሙዚቃ መሳርያ ከበሮና ጡሩንባ ሲሆን በጨዋታው ዉስጥ ሁሉ ጨዋታውን የማድመቅ ሚና አላቸው።

3.2.8.የሰርግ ቀን

ሰርጉ ሁሌም ቢሆን እሁድ ቀን የሚውል ሲሆን በእለቱ ያካባቢ ማህበረሰብ ወዳጅ ዘመድ የተጠራው ታዳሚ ሁሉ ታድሞ ምርቃት፤ለሙሽራው የስጦታ ግዜ፤ የጨዋታ ግዜ፤ የመመገቢያ ግዜያትና የእርድ ግዜ አሉት። ረጅም ሰአት የሚወስደው ግዜ ጨዋታና ጭፈራ ነው።ሲመሽም ሙሽራውና ሚዜዎቹ እንዲሁም አጃቢዎቹ በተዘጋጁላቸው ፈረሶች እየጋልቡ ሄደው ሙሽሪቱን ይዘው ወደ ሙሽራው ቤት ይመለሳሉ።አጃቢዎቹ እራታቸው ይቀርብላቸውና እየበሉ ሙሽራው ወደ ሙሽሪቱ ገብቶ ግብረ ወሲብ ይፈጽማል። ወሲቡን ፈጽመው ሲጨርሱ ሚዜዎቹ እየዘፈኑ ሙሽራውን በትክሻቸው ተሸክመውት ወደ አጃቢዎቹ ይቀላቀላሉ። ዘፈኑም

አውራጅ ጨቅላው ሸብ በል ዛሬ 2

ተቀባዮች አሆሆ እቴው ሸንኮሬ

አውራጅ ብራምባው ሰበሮሎት

ስብርብር አረገሎት

ተቀባዮች አሆሆ

አውራጅ: ጀግናው ልጆት

ተቀባዮች፡ ጨቅላው ሸብ በል ዛሬ 2

አውራጅ ለማማም ደስ ይበላቸው

ለባባም ደስ ይበላቸው

ተቀባዮች፡ አሆሆ እቴው ሸንኮሬ

አውራጅ መቶ ብር ይገባል ዛሬ

ሃምሳ ብር ይገባል ዛሬ

በቤተ ጉራጌ የሶዶ ብሄረሰብ ቋንቋ በብዛት የሚጠቅሙት የአማርኛ ቋንቋ ነው። በዚህ መልክ ሲካሄድ በነበረው ጨዋታ ላይ ከሁሉም ቤተዘመድ የደስ ደስ በሚል ሙሽራውን ተሸክመውት በሚዜዎቹ አማካኝነት ገንንዘብ ይሰበሰባል።የተሰበሰበው ገንዘብም በማግስቱ ሰኞ አጃቢዎቹ የሚታረድ ነገር ገዝተው አርደው እየበሉ ሙሽሮቹን ያስደስታሉ።

3.2.9. የብርንዶ ሰአት

ብርንዶ ከቀይ ስጋ እና የተለያዩ ቅመማቅመማት ተጨምሮበት በቂቤ ተለውሶ የሚዘጋጅ በአለም አቀፍ ደረጃ የሚታውቅ የቤተ ጉራጌ ባህላዊ ምግብ ነው። ይህም በመስቀል በአልና በተለያዩ በአላት ወቅት ይዘጋጃል በሰርግ ጊዜ ግን ሙሽራው ከሙሽሪቱ ጋር ወሲብ ፈጽመው ሲጨርሱ የጫጉላ ዘፈን ዘፍነውና ጨፍረው ከጨረሱ በኋላ ለአጃቢዎቹ የደስደስ ይቀርባል በተለይ ሙሽሪቱ ከነ ክብረ ንጽህናዋ ሙሽራው ካገኛት ልዩ ድምቀት ያለው ግብጣ ይደረጋል። ይህ የብርንዶ ሰአት ክብረ ንጽህና ለሌላት ሙሽራ ግን እጅግ ሰቀቀን ነው። ምክንያቱም ምስጢሩ ይወጣል የሆነውን ምስጢር ሁሉ ለሙሽሪት ቤተሰቦች ለናት ላባቷና በጎረቤት ሁሉ ይሰማል። ጨዋታውም አይደራላቸውም ብርንዶው ግን ለአጃቢዎች መቅረቡ አይቀርም። ከምግቡ በኋዋላ የዎርሴ ጨዋታ ይጫወታሉ። ወይዘሮ መርከብ ስለ ብርንዶ እንዲህ ብለዋል። "ብርንዶ ከምግብነት በዘለለ ለሰርጉ ስርአት ዉበትና ድምቀትም ጭምር ነው።ብርንዶ በቂቤና በተለያዩ ማጣፈጫ ቅመሞች የሚሰራ እጅግ ጣፋጭ ምግብ ነው። ብርንዶ የሌለው ሰርግ ሰርግ አይባልም።" ከላይ እንደገለጹትም ብርንዶ ለሰርጉ እጅግ አድማቂ እና በጉራጌ ማህበረሰብ ባህላዊ ምግብ ነው።

3.2.10. የሰርጉ ማጠቃለያ

የሰርጉ ማጠቃለያ እሁድ ቢሆንም ከእሁድ በኋላ ያሉ ዝግጅቶችም ሌላ ጥሩ የከተማ ሰርግ መሰርግ የሚችሉ ናችው። ለምሳሌ ብስቆት፤አውታ፤መልስ የመሳሰሉ ተጨማሪ ስራዓቶች ከፍተኛ ወጪና ጊዜ የሚያባክኑ ናቸው። በሶዶ ወረዳ አማውቱ አካባቢ የሚኖሩ ትልቅ አባት አቶ አለማየሁ ወርቁ ከሰርጉ በኋላ ስላለ ዝግጅቶች ሲናገሩ እንዲህ ገልጸውታል። "ሽባለስከ ሰርግ ካለው ጊዜ በበለጠ ከሰርጉ በኋላ ያለው ዝግጅትና ወጪው ይበልጣል። ከሰርጉ በፊት ጥሩነቱ ሰው እገሌ ሰርግ አለበት የሚለውን ያውቅለታል ከሰርጉ ኋላ ግን ሰጉን ጨርሷል አሁን ምን አለበት ሊልህ ይችላል። ከሰርግ በኋላ ያለው ወጪ ሆድ ይፍጀው።" ብለዋል ጅማሬው እጅግ ከባድ ሲሆን ማጠቃለያው ደግሞ የበለጠ ከባድ ከመሆኑ የተነሳ ማጠቃለያ የለውም

ያስብላል። የሰርጉ ሰርግነት ግን እሁድለት ምሽት ከብርንዶው በኋላ ይጠናቀቃል።በማግስቱ ደግሞ ይቀጥላል። ሙሽሪትና ሙሽራው ለመጀመርያ ጊዜ ከሙሽርነታቸው የሚወጡት መስቀል በአል ላይ ሲሆን አዳብና ጨዋታ ውስጥ ነው።

ሚዜ ጎዲን አቲዜ

ዋና ናመነ ሻኛ

ዋናናመ ጭኮኛ

አልሰጥም ካለ የሚዘፍኑበት ስድብ አዘል ዘፈን

የሚዜ አጭረ ይገቦ ተስንጭረ

ትርጉም፡ ሁለተኛ ሚዜ

ጎዲን ስጠን እንደወጋችን

ዋናው ሚዜ እንደወጋችን

ጭኮአችን ስጠን

እንደወጋችን ሻኛ አቅርብልን

3.3. የሸባል ስርአት ከሙዚቃዊ ተውኔት ንፅፅር

3.3.1.ሙዚቃ

ሙዚቃ በሙዚቃዊ ተውኔት ውስጥ ትልቅ ሚና ያለው መሆኑ አጠያያቂ አይደለም ብዙሃኑ ክፍሉም ግጥምና ሙዚቃዊ ነው። በሙዚቃዊ ተውኔት ውስጥ የድምፅ ግብዓቶች ፣ የተዋንያን ድምፅ ፣ ዘፈን በተውኔት ውስጥ ያሉ ስሜቶችን እያደመቁ ፣ የትዕይንቶች ድባብ እየመሰረቱና እያሻገሩ እንዲሁም በመሳሪያ ብቻ የተቀነባበሩ ሙዚቃዎችን በመጠቀም የሙዚቃዊ ተውኔቱን ሴራ ወደፊት በመግፋት ታሪኩን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማስፈንጠር ጥቅም ላይ ይውላሉ። በተውኔት ውስጥ ገፀ-ባህሪያት ፣ ህብረ ዘማሪያን የሚዘምሩት ዝማሬ የተውኔቱን ጊዜ ፣ የገፀ-ባህሪያትን ስሜት ፣ እንዲሁም ታሪኩ የሚፈፀምበትን ቦታ የመጠቆም አቅም አለው። በሙዚቃዊ ተውኔት ውስጥ ስለሚገኙ የዝማሬ አይነቶች ሳሙኤል ተስፋዬ

"የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር የጥናት ምርምር ጆርናል" በሚል መፅሀፍ እንዲህ ሲል ያብራራዋል።

> “በሙዚቃዊ ተውኔት ውስጥ በርካታ የዝማሬ አይነቶች ሲኖሩ ከነዚህም ውስጥ አጠቃላይ የተውኔቱን ታሪክ የሚነግሩን ተራኪ ዝማሬዎች /Narrative songs/ ዘማሪው በውስጡ ስለተሰማው ጥልቅ ስሜትና ስለሀሳቡ መረጃ የሚሰጥበት ሙዚቃ /A Musical soliloque/እና ሙዚቃዊ ተውኔት ማብቂያ ላይ ለመዝጊያነት የምንጠቀምበት /An eleven o’clock Number/ ተጠቃሽ ናቸው።” (2009፣96)

እነዚህ የዝማሬ አይነቶች በሶስት ክፍሎች ሲከፈሉ የመጀመሪያው እና መሰረት ጣይ የምንለው የዝማሬ አይነት በተውኔት ውስጥ ወደፊት ስለሚከሰተው ድባብ ማመላከት፣ ገፀ - ባህሪያቱን ማስተዋወቂያ እንዲሁም የተውኔቱን ሙድ ማሳያ ነው። ሌላኛው ተራኪ ዘማሪዎች ሲሆን ይህ የዝማሬ አይነት ገፀ-ባህሪው በውስጡ ስለተሰማው ጥልቅ ስሜት ለተጋራው ገፀ - ባህርያት ወይም ለተመልካች የሚያጋባበት የዝማሬ አይነት ነው ሶስተኛው እና የመጨረሻው የመዝጊያ ሙዚቃ ሲሆን ይህ የዝማሬ አይነት ተውኔቱ አልባሳት ላይ መድረሱን፣ ሁሉም ድራማዊ ድርጊያዎች ማብቂያቸው ላይ መድረሳቸውን የሚያሳይ የዝማሬ አይነት ነው። የሸባል ስርአትም በተመሳሳይ ሸባሉ ተጀምሮ እስኪፈጸም ድረስ ሙዚቃና ግጥም አይለየውም ለምሳሌ በእንሾሽላ ቀን፣ በቸግ ቀን፣ በእረ ቀን፣ የዎሬ እና ሌሊችም የሚቀርቡት የተለያዩ ዜማዎችን ያዘለ ነው።ስለዚህም የሸባል ስርአት ከሙዚቃዊ ተውኔት ጋ እጅግ ተመሳስሎ አላቸው ለምሳሌ እንሾሽላ፤የወሬ፤ጎሮሮ፤ኬርታና ሌሎችም ይካተቱበታል።

3.3.2. ውዝዋዜ

ውዝዋዜም በተመሳሳይ በሸባል ስርአት ውስጥ የስርአቱ የደም ስር ነው። ውዝዋዜ በሸባል ስርአት ውስጥ ብዙውን ግዜ የሚደረጉት በቡድን ነው።በግል የሚደረግ ዉዝዋዜም አለው። በክስታኔ ባህላዊ ጭፈራዎች አራት አይነት ይዘት አላቸው እነኝህም ጥልፍልፍ፤ የገሚኛ፤የምሽቲኛ እና እስክስታ ይባላሉ።ጥልፍልፍ የሚባለው የውዝዋዜ አይነት ሁለት እግርን እያጠላለፉና ትክሻ እያወዛወዙ ሁለት እጅ ወደ ፊት ዝቅ ተደርጎ የሚከወን የውዝዋዜ አይነት ነው።የገሚኛ የሚባለው የውዝዋዜ አይነት ሁለት እግርና ሁለት እጅ በተራ በተራ ወደፊት እየውረወሩ እንዲሁም ትክሻ በጋራ እያወዛወዙ የሚከወን የውዝዋዜ አይነት ነው።የምሽቲኛ

የውዝዋዜ አይነት የሴቶች የውዝዋዜ አይነት ነው፡ ሆኖም ግን ወንዶችም ይወዛወዙታል። በውዝዋዜ ወቅት ሁሉም በተራ እየተነሳ ይጨፍራል ሌሎች ደግሞ የውዝዋዜ ተራ እስኪደርሳቸው ድረስ ጨዋታውን ያደምቃሉ።

3.3.2.1 በቡድን የሚደረጉ ዉዝዋዜ

ውዝዋዜ የሚካሄደው ብዙውን ጊዜ በቡድን ነው።ሶስት ሶስት በመሆን ብሎም ሁለት ወንዶች ካሉ አንዲት ሴት መሃል ትሆናለች ሴቶች ሁለት ከሆኑ ደግሞ አንድ ወንድ መሃል ገብቶ በጋራ ይወዛወዛሉ። አንዳንዴም ብዙ መጠን ያላቸው ሰዎች በጋራ ይወዛወዛሉ።በተለይ የእስክስታ የውዝዋዜ ስልት ቡዙ ሰዎች በጋራ ይወዛወዙበታል።በመሆኑም ከሙዚቃዊ ተውኔት ጋር እጅግ ተመሳሳይነት አላቸው።

3.3.3. ሴራ

ሴራ በተውኔት ወስጥ የአንዱ ምክንያት ለአንዱ ውጤት በመሆን ወይም የግጭት እና የታርክ ውጤት በመሆን የሚፈጠር አላባ ነው። ይሁን እንጅ በሸባል ስርዓት ውስጥ ሆን ተብሎ የሚሰራ ወይም የሚፈጠር ሴራ እና ግጭት ባይኖርም ነገር ግን የድርጊቶች ቅደም ተከተል በሰፊው ይገኙበታል። በሸባል ስርዓት የሚከወኑ ድርጊቶች ሁሉም ምክንያታዊ በመሆን በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀምጠዋል። ከዚህ በመነሳት የሸባል ስርዓት ውስጥ የድርጊቶች ቅደም ተከተል መኖራቸው በውስጡ ሴራ መኖሩን ያመላክታሉ። በሸባል ስርአት ውስጥ ሴራ ትልቅ ቦታ አለው ። የወንዱ ቤተሰብ ለልጃቸው የፈለጉትን ልጃ ገረድ ለማግኘት እሺታ እስኪያገኙ ድረስ ብዙ ውስብስብና ግጭት ቀስቃሽ ሁኔታዎች ሴራዎች ይከሰታሉ።ስለዚህም በቤተ ጉራጌ የሰርግ ወይም ሸባል ስራት ውስጥ ሴራ ጉልህ ሚና አለው።

3.3.5.ጭብጥ በሸባል

ጭብጥ በሸባል ስርዓት ውስጥ ስንመለከት በውስጡ በቅደም ተከተል ከሚያስቀምጣቸው እና በውስጡ ካሉት ድርጊቶች እና ታሪኮች በመነሳት ማዕከላዊ የሆነውን ሀሳብ ከታሪኩ ፍሰት አንባር ዓብይ ጭብጥ እና ንዑስ ጭብጥ ብለን መለየት እንችላለን።

3.3.6.ዓብይ ጭብጥ

የሸባል ስርዓት ዋናው ወይም ዓብይ ጭብጥ ጋብቻ ወይም ትዳር ነው።

3.3.7.ንዑሳን ጭብጥ

በሸባል ስርአት ውስጥ የተለያዩ ንዑሳን ጭብጦች የሚገኙ ሲሆን እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፦ ባህልን ማሳወቅ፣ ባህሉን መጠበቅ፣ መተሳሰብ እና መከባበር እንዲሁም ፍቅር የመሳሰሉት በሸባል ስርዓት ውስጥ የሚገኙ ንዑሳን ጭብጦች ናቸው። ከዚህ በመነሳት አጥኚው ከዚህ ሀሳቦች በመደገፍ ከላይ የተገለፀውን የጭብጥ አይነት ከጭብጥ ባህርያት አንፃር በመነሳት አካባቢያዊ ጭብጥ እና ከሁለንተናዊ ጭብጥ ለማየት ችሏል።

3.3.8.ገፀ-ባህርያት በሸባል

በሸባል ስርዓት ውስጥ የተለያዩ ገፀ-ባህሪያት የሚገኙ ሲሆኑ ዋና አቀንቃኞች ሁለቱ ሙሽሮች ናቸው። ጫንያለው ወልደ ጊዮርጊስ፣ አስታጥቃቸው ይሁን፣ ተስፋዬ ገብረማርያም፣ እቴነሽ ካሳ፣ አለማየሁ ታደሰ በጻፉት መሰረታዊ የተውኔት አጻጻፍ መርሆች በሚል መጽሃፍ ስለ ገጸ-ባህርያት እንዲህ አስቀምጠዋል። "የአብዛኛዎቹ ገጸ-ባህርያት መነሻ በውነተኛው ህይወት ውስጥ የሚመላለሱ እውነተኛ ሰዎች ናቸው። ይሁንና የእውነተኛ ህይወት መነሻ እናድርግ እንጂ ከህይወት የምንወስደው ነገር ገደብ አለው።" (2006፣16) ከላይ እንደተገለጸው ገጸ ባህርያቱ እንደየ ገጸ ባህርያቱ የተለያየ ደረጃ አላቸው። ሙሽሮች በባህሉና ከላይ በተዘረዘሩት ስርአቶች መሰረት የተጫጩት ሲሆኑ ሌሎች ብዙ ገጸ ባህሪያት ይታደሙበታል የሙሽሪት እናትና አባት፤ የሙሽራው እናትና አባት፤በሁለቱም ሙሽሮች በኩል የሚቀመጡ ሚዜዎች ፤ መራቂ ያካባቢ ሽማግሌዎች በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ሙሽራው

ሙሽራው እድሜው ለጋብቻ የደረሰ ሙሽሪቱን የሚያገባ ዋናው ገጸ ባህሪ ነው።

ሙሽሪት

ሙሽሪቱ እድሜዋ ለጋብቻ የደረሰች ሙሽራውን የምታገባዋ ዋናዋ ገጽ ባህሪ ነች።

የሙሽሪት እናትና አባት ወይም አሳዳጊ

የሙሽሪት ወላጆች ከመውለድ ወይም ከማሳደግ እስከ መዳር ሰርጓን በበላይነት ይዞ መወጣትና ሙሽሪቱን ለባሏ ቤተሰብ እስኪያስረክቡ ሁኔታውን መፈጸም ነው።

የሙሽሮቹ ሚዜዎች

ሚዚዎች በሁለቱም በኩል በስራቸውና በሰርጋቸው ሂደት ሁሉ እስከፍጻሜ አብረው በማገዝ ከጎናቸው የሚቆሙ ጉዋደኞቻቸው ሲሆኑ በወንዱ በኩል ሁለት ሚዜ ዋናና ተከታይ ሚዜ ይኖሩታል።በሙሽሪትዋ በኩልም ሁለት ሴት እኩዮች ሚዜ ሆነው የሚቆሙ ናቸው።

የሃገር ሽማግሌዎች

እድሜአቸው የገፉ ያካባቢ ሽማግለዎች "ኬር" ይላሉ ይመርቃሉ ያስማማሉ በየመሃሉ ይሸኛሉ ችግር ሲያጋጥም እርቅ ያወርዳሉ የሃገር ሽማግሌዎች ከፍተኛ ሚና አላቸው። በመሆኑም የሸባል ስርአት ገጸ ባህሪ ንፅፅር ሲታይ በብዙ ይመሳሰላል።የሚለያቸው ደግሞ ሙዚቃዊ ተውኔት ቃለ ተውኔት ተጽፎ ተጠንቶ የሚቀርብ ሲሆምን የሸባል ስርአት ግን ድንገቴ ፈጠራን ይጠቀማሉ ቴክኒካል ለሆኑ ነገሮች ለማሙዋላት በሸባል ስርአት ውስጥ ትኩረት አይሰጠውም።ሙዚቃዊ ተውኔት የፈጠራ ስራ ሊሆን ሲችል ሸባል ግን የሰው ልጅን እውነተኛ ሂዎት የሰርግ ኩነት የሚታይበት ነው።

3.3.9 አልባሳት

አልባሳት የቴአትር አላባ ሲሆን ተዋናዩ የሚለብሱት ልብስ ነው። በመደበኛው ቴአትር (ድራማ) የተወኔቱን ዘውግ፣ የተዋናዬቹን ምንነት የምንገልፅበት ነው። የትውፊታዊ ተውኔት አልባሳት እንደየማህበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ፣ባህልና ወግ የሚለያይ ነው። አልባሳት አንዱ የቲያትር አላባ ሲሆን ገፀ-ባህሪያቱ የሚለብሱት ልብስ ነው። በመደበኛው ቲያትር ወይም ድራማ የተውኔቱ ዘውግ፣ የማህበረሰቡ አኗኗር፣ ምጣኔ ሀብት፣ የተዋንያኖቹ ማንነት የሚታይበት ነው። የትውፊታዊ ተውኔት አልባሳት የአንድ ማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ፣ ባህል፣ ወግ፣ ሀይማኖት እና የማህበረሰቡን ተግባቦት የሚለይ ነው። ይህንን አስመልክቶ ፋንታሁን እንግዳ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው በሚለው መፅሀፍ ላይ እንዲህ ሲል ያስቀምጣል።

" አልባሳት ተዋንያን ዝግጅታቸውን ለተመልካች በሚያቀርቡበት ጊዜ

የሚለብሱት ልብስ መጠሪያ ነው። አልባስ የሚለው ቃል ምንጩ

ከቤተ-ክርስቲያን ሲሆን ጳጳስ፣ ቀሳውስት እና ዲያቆናት በ ክብረ

በዓላት እንዲሁም ለስረዓተ ቅዳሴ ወደ ቤተ ክርስትያን በሚገቡበት

ጊዜ የሚለብሱት እና የሚዘረጉትን ጃንጥላ ይጨምራል። አልባሳት

ጊዜ እና ቦታን፣ የኑሮ ደረጃን፣ እምነትን፣ፆታን፣ የሙያ መስክን፣

የግላዊ ፀባይን እና የንቃተ ህሊና ደረጃን ሳይቀር ሊወክሉ

እና ሊያንፀባርቁ ይችላሉ።"/ፋንታሁን እንግዳ፣ 2001 ዓ.ም፣ 92/

በመሆኑም በሶዶ ክስታኔ ባህላዊ የሰርግ ስርአት የሚጠቀሙት አልባሳት ሙሉ ነጭ ልብሶች ሙሽሮች ይለብሳሉ፤መራቂ ሽማግሌዎች ጋቢ ፤ ሚዜዎች በመረጡት መልክ ተመሳሳይ አልባሳት ፤ እናቶችና ሙሽሪት ሻሽ፡ መቀነት ፤ ሙሽራዎቹን የሚሸከሙት ፈረሶች ኮርቻ ይለብሳሉ። አልባሳቱም ሰርጉን ከሚያደምቁት ሁኔታዎች አንዱና ባልባሳት ደረጃም ከአልባሳት አጻር የተሟላ

3.3.10 ቃለ- ተውኔት

ቃለ ተውኔት ሁለት እና ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው ገፀ-ባህሪያት በተውኔት ድርሰት ውስጥ እርስ በእርሳቸው የሚያወሩት የምልልስ ንግግር ነው። በገፀ-ባህሪያት መካከል የሚደረግን ምልልስ ዘሪሁን አስፋው "የስነ-ፅሁፍ መሰረታውያን" በሚል መጽሐፉ እንዲህ ሲል ያብራራዋል።

> “ምልልስ በዘዴነቱ የገፀ-ባህሪያትን ስሜት ፣ አላማ፣ ችግር እንዲሁም ስነ-ልቦናዊ መልስ ማሳያ በመሆኑ ተሳታፊ ገፀ-ባህሪያት ያላቸውን የእርስበእርስ ግንኙነት ለማሳየት ይጠቅማል። በገፀ-ባህሪያት መካከል የሚደረግ ምልልስ ለምልልስነቱ ወይም ሁለቱ ገፀ-ባህሪያት ንግግር እንዲለዋወጡ ብቻ ለማድረግ የሚፈጠር አይደለም።” (2004 ፣ 205)

ከላይ እንደተገለጸው ቃለተውኔቶች እያንዳንዳቸው የሚፈጥሩት ስሜትና የሚገልጹት የሚያስተላልፉት መልክት ሲሆን ሙዚቃዊ ቴአትር አብዛኛውን የሚጠቀመው ግጥማዊ በመሆኑ በሸባል ስራት ውስጥ ያለው ቃለት ተውኔቶች የሙዚቃዊ ተውኔት የቃለ ተውኔት አላባን ያሟላ ነው።

3.3.11 ቁሳቁስ

በተውኔት ውስጥ ቁሳቁስ ማለት ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸው የሚፈጠሩ ሳይሆኑ ያሉና የሚኖሩ ቁሳቁሶችን ማህበረሰቡ ለትውፊቱ ሲል የሚጠቀምባቸው ናቸው። ቁሳቁስ ማለት በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ ከዋኞች የሚጠቀሙባቸው ማንኛውም አይነት እቃዎች ናቸው።

በቁሳቁስ ከዋኞች በክንዋኔው ውስጥ ያላቸውን ሚና እና ማንነታቸውን በቀላሉ ለተመልካች ሆነ ለተሳታፊው ሊያሳውቃቸው ወይም ሊያስረዳቸው ይችላል። ይህም ከዋኞች የሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ለትውፊት መከወኛ ወይም ትውፊትን ለማከናወን የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች ሲሆኑ ቁሳቁሶቹም ባህለዊ መሆናቸውን ያስረዳል። ይህን በማስመልከት "A preliminary investigations of Dramatic element with in traditional ceremonies›› አቦነ አሻግሬ እንደሚከተለው ገልፆታል ::"ቁሳቁስ ማለት በትውፊተዊ ተውኔት ውስጥ ከዋኞች የሚጠቀሙባቸው ማንኛውም አይነት እቃዎች ማለት ነው። በቁሳቁስ ከዋኞች በክዋኔው ውስጥ ያላቸውን ሚናእና ማንነታቸውን በቀላሉ ለተመልካችም ሆነ ለተሳታፊውሊያሳውቅ እና ሊያስረዳ ይችላል።"/ አቦነ አሻግሬ፣ 1984፣13ዓ.ም ይህም ማለት ከዋኞች የሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ለትውፊቱ መከወኛ ወይም ትውፊቱን ለማከናወን የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች ሲሆኑ ቁሳቁሶቹም ባህላዊ የሆኑ መሆናቸውን ያስረዳል።በክስታኔ ሰርግ ትውፊት ዉስጥ ቁሳቁስ በብዛት የሚጠቀሱ ናቸው። ብሎም አገልግል ፤ የሙሽሪት ሊብሶች ፤ በከብት ቆዳ የሚሰራ የፈረስና የሙሽሪት መግረፊአ አለንጋ ፤ እርጥብ ቁጤማ ፤ የሙሽሪት እናትና አባቶች ልብስ ገንዘብ ተጠቃሽ ሲሆኑ የሽባል ስርአት ናቸው።

3.3.12. መቼት

በተውኔት ውስጥ መከናወኛ ቦታ መቼት የሚለውን ጊዜና ቦታን የሚወክል የተውኔት አላባ ነው። መቼት የአንድ ተውኔት ፣ልብወለድ፣ የግጥምና የፊልም ታሪክ የሚከናወንበት ቦታ፣ ጊዜና ማህበራዊ እውነታ ነው። መቼት "መቼ" እና "የት" የሚሉትን ቃላት የያዘ ሲሆን ትርጉሙም ተውኔታዊ ጊዜው የሚከናወንበት ቦታና ጊዜ ያመለከተናል። የሽባል ስርአትም የሚካሄድበት ጊዜና ቦታ ሙሽሮች የሚሞሸሩት በተለያየ ጊዜ በተለያየ ዘመዳቸው ቤት ነው። ብዙ ጊዜ የሽባል ስርአት የሚከወነው ሁዳዴ ጾም ከተፈታበት ሰአት ጀምሮ ይከወናል። እያንዳንዱ ስርአት በዚህ መልክ የተለያየ ጊዜና ቦታ አለው። ስለሆነም ከጊዜና ቦታ አንጻር የሽባል ስርአት ሙሉ በሙሉ የተሟላ ነው።

በተጨማሪም ዘሪሁን አስፋው የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን በሚለው መፅሀፍ ላይ እንዲህ ሲል አስቀምጧል ፡-

" መቼት ታሪክ የተከናወነበት እና ገፀባህሪያቱ የሚኖሩበት

ወይም የኖሩበትየገጠር ቦታ ወይም የከተማ አከባቢ

ብቻ አይደልም። አያሌ ነገሮችን ይጨምራል። ከገጠሩ

እና ከከተማው ህይወታዊ እንቅስቃሴ ጋር ያሉትን

የተለያዩ አካተው በመያዙ ጓዘ ብዙ ነው።።"

ዘሪሁን አስፋው፣ 2004፣ 170 ዓ. ም፣

በማለት ገልጸታል። የሶዶ ክስታኔ ማህበረሰብ የሰርግ ስነ አርአት መከወኛ ቦታን አስመልክቶ አቶ እንዳልካቸው ግዛው የሶዶ ወረዳ ባህል እና ቱሪዝም ሀላፊ ሲገልፁ፡-*"የክስታኔ የሰርግ ስነ-ስርዓት የሚከወነውከሚያዝያ ብሎም አጋዴ ጾም ከተፈታበት ጊዚ ጀምሮሲሆን ቀኑም በአብዛኛው ጊዜ እሁድን በመጠቀም በየመኖሪያ ቤታቸው ዳስ በመጣል ይከወናል።"* በማለት ገልጸውታል።ይህም ማለት በማህበረሰቡ የሰርግ ስነ-ስረዓት የሚከወነው እሁድ ሲሆን የማህበረሰቡን የእረፍት ቀን ተንተርሶ የሚደረግ መሆኑን ይገልፃል። በማለት ያስረዳሉ። የክስታኔ የሸባል (የሰርግ) ስነ-ስረዓት የሚከወነው ከሚያዝያ ወር ጀምሮ በየ ጎጇቸው መከወኑ ቦታና ጊዜውን ያሚላ መሆኑ ያሳያል።

ምዕራፍ አራት

4.ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳቦች

4.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በጉራጌ ዞን ሶዶ ክስታኔ ማህበረሰብ የሸባል ስርአት ከሙዚቃዊ ተውኔት አንጻር በሚል ርእስ ተነስቶ የተሰራ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው። ከሰርጉ ጅማሬ ከቅድመ ዝግጅት ከቸግ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ሸባል (የሰርግ) እለት ድረስ በርካታ ዎጪዎችን የሚጠይቁ ዘርፈ-ብዙ ስርአቶችን ያቀፈ ነው። የሶዶ ጉራጌ ማህበረሰብ የሰርግ ስርአት ከሙዚቃዊ ተውኔት አንጻር የሚተነትን ጥናታዊ ጽሁፍ ሲሆን የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዋና አላማ በጉራጌ ዞን በክስታኔ ማህበረ-ሰብ የሰርግ ስርአትን ዳሷል። በሶዶ ጉራጌ የክስታኔ ማህበረሰብ የሸባል [የሰርግ] ስነ- ስርአት ላይ ምን አይነት ክዋኔዎች ይከወናሉ? ለሚለው ጥያቄ መልስ ተሰጥቶበታል። የሰርግ ስርአቱ ሲካሄድ የሚከወኑ ክውኖችን ዳሰሳ አድርጓል። ይህንንም ከሙዚቃዊ ተውኔት ንፅፅር ተንትኗል ፤ በትውፊቱ ከሚከወኑት ክውኖች የሰርጉ ይዘት ፣ የሽማግሌዎች ምርቃት ፣ ጨምሮ ዳሿል። አጥኚው በአከባቢው ከሚገኙት ትውፊቶች መካከል የሶዶ ጉራጌ የሸባል ወይም የሰርግ ስነስረዓት በመውሰድ ከሙዚቃዊ ተውኔት ይዘት በውስጡ ይዟል ወይስ አልያዘም ለማለት ጥናቱን ካጠና በኋላ የሶዶ ጉራጌ የሰርግ ስነ-ስረዓት የሙዚቃዊ ተውኔት አላባውያንን ሙሉ በሙሉ በተገቢው መንገድ አሟልቶ አግኝቶታል።

4.2. የመፍትሄ ሃሳቦች

ስርአቱንና በአካባቢው የሚገኙ ቅርሶችን ማስተዋወቅ ለብሄሩ ብሎም ለሀገሪቱ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው የላቀ በመሆኑ እየጠፉ የሚገኙትን ትውፊቶችን ለማቆየት በሰነድ ቢሰነዱ ፣ በመጻህፍት ቢጻፉ ፣ በኪነ-ጥበብ ዘርፋት ተሰርተው ለሌላ ብሄረሰቦች ቢቀርቡ ፣ ባህሉን ጠብቆ የማቆየት መፍትሄዎችን አስቀምጧል። አጥኚው ጎጂ ከሆኑት ባህሎች መካከል ደግሞ ጥፍር ቀፈፋ ፣ መጠኑ ያልተለካ ኮሶ መጠጣት ፣ ለሰርጉ ከፍተኛና ከአቅም በላይ ወጪ ማፍሰስ እንዲቀንስ ማድረግ የሃገሪቱ መንግስትና የዞኑ ባህልና ቱሪዝም ለብሄረሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ በኪነጥበብ መልክ ቢሰጥ መፍትሄ ይሆናል ብሎ ጠቁሟል። ታሪክ ለስነ-ጥበብ፣ ለሳይንሳዊ ጥናት እና ምርምር ትልቅ ድርሻ አላቸው በማለት ያስቀመጣቸው እንደ

ጢያ ትክል ድንጋይና የመስቀል በአል ተጠቃሽ ናቸው። ስለዚህ በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎች እነዚህን የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶችን ለመጎብኘት ወደ ስፍራው በሚሄዱበት ጊዜ የሸባል ስርአት መልካም ገጽታዎችን በሙዚቃዊ ተውኔት ቢሰራና ለሌላው ማህበረሰብ ማስተዋወቅ ቢቻል አለምን ሊረዳ የሚችል ባህል ወይም ስርአት ማስገንዘብ ይቻላል።በዚህ ብሄረሰብ ዉስጥ አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት ብሎም አንድ ለአንድ መሆን ትልቅና ታላቅ! ህግ ነው። ለሌሎች ዜጎች ትልቅ መማርያ መሆን የሚችል ትውፊት ነው። አሁን ግን ባህሉ እየተሸረሸረ መሆኑን ያካባቢው ሽማግሌዎ ለአጥኚው አሳውቀዋል። አጥኚውም በኪነ-ጥበብ መልክ ትውፊቱን ለማቆየት መሰነድ እንደ ዋነኛ መፍትሄ አስቀምጧል።

ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

All musical consists of sertain key elements; music,books,cherography,staging,physical, prodaction.

ዋቢ-መጻህፍት

መልዓከ ሰላም ዳኛቸው ::ትውፊት እና መንፍሳዊ ህይወት:: አዲስ አበባ ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት 200ዓ.ም4::

መንግስቱ ሃይለማርያም፣ድንበሩ አለሙ፣ፍቅሬ ሃይለማርያም፣ተስፋዬ መኩርያ፣ተዘራች ቢረዳ፣ ግርማ ጥላሁን፣ምትኩ ተሾመ::ጎንት::1987 ዓ.ም

መጽሃፍ ቅዱስ :: የኢትዮጵያ መጽሃፍ ቅዱስ ማህበር:: [ዘፍጥረት 1:27] 1997 ዓ.ም ::

ሳሙኤል ተስፋዬ :: የመድረክ ጀርባ ጥ በባት :: አዲስ አበባ ፣ ንግስት ማተሚያ ድርጅት ፣ 2010 ዓ.ም ::

አያልነህ ሙላቱ :: ደረጃ ሙዚቃዊ ድራማ :: ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ፣ 19861 ዓ.ም ::

ዘሪሁን አስፋው :: የስነ - ፅሁፍ መሰረታው ያ ን :: አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርጅት ፣ 2004 ዓ.ም ::

ያለው እንዳወቅ ሙሉ:: ቤተ ክርስትያንህን እወቅ:: አዘጋጅ እና አሳታሚ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስትያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማህበረ ቅዱሳን:: አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም::

ዲቆን ሄኖክ ሃይሌ :: ቤተ ክርስትያንህን እወቅ :: አዲስ አበባ ፤ ዮዳሄ ማተሚያ ፣ 2001 ዓ.ም ::

ጆን ኬንሪክ ፣ musical teatre hisyory በተሰኘው መጽሃፉ ላይ የሙዚቃዊ ተውኔት አላባውያንን በማለት አስቀምጧል:: "ሙዚቃ፣ሴራ፣ ውዝዋዜ ፣ ዝግጅት ፣ ቴክኒካል ግብአት ናቸው::" (2008,15)[1]

ጫንያለው ወልደ ጊዮርጊስ ፣ ተስፋዬ ገ / ማርያም ፣ አስታጥቃቸው ይሁን ፣ እቴነሽ ካሳ ፣ አለማየሁ ታደሰ መሰረታዊ የተውኔት አጻጻፍ መርሆች 2001 ዓ.ም::

አቦነ አሻግሬ "A preliminary investigations of Dramatic element with in traditional ceremonies› *1984፣13 ዓ.ም* ::

ጌታቸው በለጠ :: የጥበባት ጉባኤ :: አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተምያ ፣ 2004 ዓ.ም ::

ፍቃደ አዘዘ ። የስነቃል መመርያ ። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተምያ ፣ 1991 ዓ.ም ።

ፋንታሁን እንግዳ ። የተውኔት ድርሰት አጻጻፍ ዘዴ ። አዲስ አበባ ፣ ብርሃኒና ሰላም ማተሚአ ቤት ፣ 2009 ዓ.ም

ፒተር ሀሮፕ እና አቦነህ አሻግሬ ። A Preliminary investigation of dramaticelements with in traditional cerimonies, ። 1984 ዓ.ም ።